ጅማ ዩኒቨርሲቲ
ሶሻል ሳይንስና ሂማኒቲስ ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋናሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የጠምባርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሑፍ ላይ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና፤ በጠምባሮ ልዩ ወረዳ ሦስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ
ዘካርያስ ኢሳያስ

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ድግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ሰኔ 2016 ዓ.ም
ጅማ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂማኒቲስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋና/ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የጠምባርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሑፍ ላይ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና፤ በጠምባሮ ልዩ ወረዳ ሦስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

ዘካርያስ ኢሳያስ

አማካሪዎች:- ምህረት ሳደሞ (ዶ/ር)

ማንያለው አባተ(ዶ/ር)

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ድግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ሰኔ 2016 ዓ.ም

ጅማ

## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

የጠምባርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና በሚል ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ በድህረ-ምረቃ ኘሮግራም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ በማስተማር ስነ-ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ በዘካርያስ ኢሳያስ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈተና ቦርድ አባላት ተረጋግጧል፡፡

የአማካሪ ስም: ------------------------- ፊርማ------------ቀን----------------

የውስጥ ፈታኝ ስም:----------------------ፊርማ------------ቀን-------------

የውጭ ፈታኝ ስም:- -------------------------ፊርማ------------ቀን----------

# ምስጋና

በቅድሚያ በነገር ሁሉ የረዳኝን ልዑል እግዚያብሄርን አመሰግናለው፡፡ በመቀጠል በተጣበበ ጊዜ ያለመሰልቸት ስህተቶቼን እያረሙ፣ እያበረታቱ እና ተስፋ እየሰጡ ለዚህ ውጤት ያበቁኝን አማካሪዎቼን ዶ/ር ምህረት ሳደሞን እና ዶ/ር ማንያለው አባተን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም ባለው አቅም በባጀት በመደገፍ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ከግብ እንዲደርስ ድጋፍ ላደረጉልኝ ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በስራዎቼ ሁሉ መረጃ በማሰባሰብ፣ በማረምና በማደራጀት ለረዳችሁኝ ለእስታፍ አባላቶቼ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለው፡፡

## አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ጠምባርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሑፍ ላይ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶችና የስህተት ምንጮችን መመርመር ነው። ተጠኚ ተማሪዎቹ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በጠምባሮ ልዩ ወረዳ በሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ጠምባርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች ናቸው።  በጥናቱ የተካተቱት 102 ተማሪዎች ሲሆኑ የተመረጡትም በቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ ነው።  ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት በተጠኚ ተማሪዎቹ በሁለት ዙር 204 ድርሰቶች እንዲጽፉ ተደርጓል። በነዚህ ድርሰቶች መሰረት ተማሪዎቹ በጽሑፋቸው ላይ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ለመለየት ተችሏል። በተጨማሪም ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽሑፍ መጠይቆች መረጃ ተሰብስቧል። በነዚህ መረጃዎች ለተማሪዎች ስህተት መፈጸም ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ለመለየት ተሞክሯል። ከድርሰት እርማት በተገኘው መረጃ መሰረት ጠቅላላ የስህተቶች ብዛት 1851 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 912 (49.27) የቋንቋ አጠቃቀም፣ 619 (33.44%) የሥርዓተነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች እና 320 (17.28%) የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች ሆነው ተገኝተዋል። ተማሪዎች ከጻፏቸው ድርሰቶች እንዲሁም በመምህራን ከተሞሉ መጠይቆች በተገኙ መረጃዎች መሰረት የስህተቶቹ ምንጮች የማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅትና የማስተማሪያ ዘዴ ድክመት እንድሁም የስነልቦናዊ ሁኔታዎች ተጽእኖ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። እነዚህን ችግሮች ለማቃለል የማስተማሪያ መሳሪየዎችን አዘገጃጀት እና የማስተማሪያ ዘዴዎችን ማሻሻል፤ እንዲሁም ተማሪዎች ትምህርቱን በፍላጎት እንዲማሩ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሚሉ መፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመዋል።*

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ምስጋና ....................................................................................................................................i
አጠቃሎ................................................................................................................................... ii
ማውጫ ................................................................................................................................... iii
ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ ............................................................................................................1
1.1 የጥናቱ ዳራ ...........................................................................................................................1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..........................................................................................................3
1.3 የጥናቱ ዓላማ ........................................................................................................................4
1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ .................................................................................................................4
1.4 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች .............................................................................................................4
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ......................................................................................................................4
1.6 የጥናቱ ወሰን..........................................................................................................................5
ምዕራፍ ሁለት፤ክለሳ ድርሳናት....................................................................................................6
2.1.ንድፈ-ሀሳባዊ ቅኝት....................................................................................................................6
2.1.1.የስህተት ምንነት.....................................................................................................................6
2.2 የስህተት ትንተና ምንነት .........................................................................................................7
2.3 የስህተት ምንጮች.....................................................................................................................8
2.3.1 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ ......................................................................................................8
2.3.2 የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ .............................................................................................................9
2.3.3 የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት .........................................................10
2.3.5. የመጻፍ ክሂል ያለበት ደረጃ ..................................................................................................12
2. 4. መጻፍ ለምን አስቸጋሪይሆናል? ............................................................................................12
2.4.1 ስነ-ልቦናዊ ችግር.................................................................................................................12
2.4.2 ሰዋስዋዊ ችግር ....................................................................................................................13
2.4.3 የግንዛቤ ችግር......................................................................................................................13
2.5 የስህተት ትንተና ማካሄድ ጠቀሜታ .........................................................................................13
2.6 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት.........................................................................................................15
ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ዘዴና አካሄድ .........................................................................................18
3.1 የአጠናን ዘዴ ........................................................................................................................18
3.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ..........................................................................................18
3.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ...............................................................................................18
3.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ..................................................................................................19

3.5 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ....19
3.6 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ....19
3.6.1 ድርሰት ማፃፍ ....19
3.6.2 መጠይቅ ....20
3.6.2.1. የመምህራን መጠይቅ ....20
3.7 የመረጃ አተናተን ....20
3.7.1 የመጠይቆች አተናተን ....20
3.7.2 የድርሰት ፈተና አተናተን ....20
3.5.2 የመጠይቆች አተናተን ....22
ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተና ....23
4.1 በድርሰቶቹ ውስጥ የታዩ አጠቃላይ የስህተት ብዛት ....23
4.2 የስህተቶች ስርጭት....24
4.2.1 የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ....25
4.2.1.1 የሆሄያት ቅርጽ ስህተት ....26
4.2.1.2 ግድፈት ....28
4.2.1.3 የቃላት ድግግሞሽ....29
4.2.1.4 ያልተለዩ ስህተቶች ....30
4.2.2 የቋንቋ አወቃቀር ስህተት....30
4.2.2.1 የዓረፍተ ነገር ስምምነት ስህተት ....31
4.2.2.2 የመስተዋድድ እና የተሳቢ አገባብ ስህተት....32
4.2.2.3 የቃላት አጠቃቀም ስህተት ....33
4.2.3 የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት....34
4.2.3.1 የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት....35
4.2.3.2 የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተት ....35
4.3 የስህተት ምንጭ መላምቶች ....36
ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያና የመፍትሄ ሐሳብ....41
5.1 ማጠቃለያ ....41
5.2 የመፍትሄ ሀሳብ ....43
ዋቢ ጽሑፎች....44
አባሪዎች....46

# ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ አንድ የትምህርት አይነት መሠጠት የተጀመረው ዘመናዊ ትምህርት በፊት በተለይ በአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ-መንግስት ወንጌልን ለማስተማር ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ሚስዮናውያን በተለያዩ አካባቢዎች ትምህርት ቤቶችን እንዳቋቋሙ፤ በነዚህም ባቋቋሟቸው ትምህርት ቤቶችም ውስጥ ከሚሰጡት የትምህርት አይነቶች መካከል አንዱ አማርኛ ነበር(ዮናስ እና ሌሎችም 1966፣42):: ዘመናዊ ትምህርት ሲጀመር(በ1940ዓ/ም አካባቢ) ለመጀመሪያ ጊዜ በተቀረጸው የአንደኛ ደረጃ ስርዓተ-ትምህርት ውስጥ አማርኛ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ተካቶ እንዲሰጥ ተደርጓል። ይህ ስርኣተ ትምህርት በተምህርት አይነቶች ውስጥ የሚተኮርባቸውን ይዘቶች ለይቶ በማስቀመጥ በ1951 ዓ.ም ተሻሽሎ ሲቀርብም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በተመለከተ ከተካተቱት የትምህርት ይዘቶች መካከል አንዱ ድርሰት (ጽህፈት) ነበር(ልኡልሰገድ፣ 1997)::

ከአራቱ መሠረታዊ የቋንቋ ክሂሎች መካከል አንዱ የጽህፈት ክሂል ነው:: የመጀመሪያ የቋንቋ ተናጋሪዎችም ሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በመደበኛው ትምህርት ቤት ውስጥ ይማሩታል:: በሁለተኛ ቋንቋ ለመጻ ወቅት ጽህፈትን ተጠቅሞ ሀሳብን ለመግለጽ የቋንቋውን ሰዋስው ማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ማወቅ ያስፈልጋል:: ጽህፈት እንደ ማዳመጥና መናገር ክሂሎች ለቋንቋው ተጋላጭ በመሆን ብቻ የሚገኝ ሳይሆን አፍ-ፈትም ሆኑ ኢ-አፍ-ፈት ተናጋሪዎች በሚያደርጉት ተደጋጋሚ ልምድና ትምህርት የሚዳብር ነው:: በዚህም የተነሳ የጽህፈት ክሂልን የሚማሩ ተማሪዎች በርካታ ስህተቶችን ይፈጽማሉ:: በተጨማሪም አንድ ሰው በጽህፈት አማካይነት ለመግባባት ሲያስብና የሚፈልገውን መልእክት ለተቀባዩ ለማስተላለፍ ሲፈልግ እንደ መናገርና ማዳመጥ ክሂሎች አጋዥ ስሜታዊና አካላዊ መግለጫዎችን ለምሳሌ፦ የፊት ገጽታ፣ ፈገግታ፣ ቁጣ፣ የድምጽ ጫና፣ የንግግር መደጋገም የመሳሰሉት ነገሮች አይኖሩም(መጠቀም አይችልም):: ከዚህም የተነሳ ጸሓፊው የሚያስተላልፈው መልእክት ለተቀባዩ ግልጽ እንዲሆንለትና የሚያሻሙ ነገሮችን ለማስቀረት ተማሪዎቹ ጽሕፈት ከመጻፋቸው በፊት ጥንቃቄ የተሞላበት ዝግጅትና በቂ ልምምድ እንደሚያስፈልጋቸው ይታመናል Norrish(1992):: ይሁን እንጂ ጽሕፈት ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ቢታዩበትም የሰው ልጅ ሀሳቡን ለሌሎች ቀርጾ ለማቆየትና ለማስተላለፍ ይችል ዘንድ የጽህፈት ክሂል ትምህርት እንደሚያስፈልገው ይታመናል:: በጽህፈት አማካይነት የሚደረግ የቋንቋ ግንኙነትም በዋነኛነት የትምህርት ውጤት በመሆኑ ከፊደል አጣጣል ጀምሮ የቃልን፣ የሀረግን፣ የአረፍተነገርን፣ የአንቀጽንና የድርሰትን አወቃቀር በየደረጃው መማር ክህሉን ጠንቅቆ ለመረዳት አስፈላጊ ነው:: የጽሑፍ ክሂል የቋንቋ ትምህርቶች አቢይ መሠረት የሆነውም በዚህ ምክንያት ነው::

አማርኛ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርትነት ከሚሰጥበት አጣቃላይ አላማዎች አንዱ ተማሪው የቋንቋውን ስርኣት ጠብቆ ድርሰት፣ ደብዳቤ፣ ሪፖርት ወዘተ መጻፍ እንዲችል ለማድረግ ነው(የትምህርት ሚኒስቴር 1970)። ይሁን እንጂ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሑፍ አቀናብረው መልእክት ለማስተላለፍ የተለያዩ ችግሮች ያሉባቸው መሆኑ በስፋት ይነገራል። ይህንኑ የጽህፈት ችግር በሚመለከትም ባዬ(1987፣8 ) ቀደም ሲል ይሰጥ የነበረው የቋንቋ ትምህርት በሰዋስው ላይ ያተኮረ እንደነበረና በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በክሂል ዘርፎች ላይ እንዳተኮረ ገልጸው፤ ሆኖም ግን የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጽህፈት በሚታይበት ጊዜ እንኳንስ ትምህርታቸውን ያልጨረሱት ቀርቶ አስረሁለተኛን ያጠናቀቁትም ቢሆኑ ሌለው ቢቀር የማመልከቻ ደብዳቤ መጻፍ የማይችሉበት ደረጃ እንደ ደረሱና በጥቅሉም ተማሪዎች ከቋንቋ ስርዓትም ሆነ ከክሂሉ እንደሌሉበት ገልጸዋል። ሆኖም ይህ ችግር በኢትዮጵያ ብቻ የሚታይ አለመሆኑን የሚያረጋግጡ የተለያዩ የውጪ ሀገር የቋንቋ ምሁራን በጽሑፎቻቸው ያስነብባሉ። ይህንኑ ሀሳብ አስመልክቶ Rechards(1992፣ 100) በዩኒቨርሲቲ ደረጃ እንኳን ብዙዎቹ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ በተማሩት መሰረት በጥሩ ሁኔታ ሲጽፉ አይታዩም፤ ቁጥራቸው ይህ ነው የማይባል ተማሪዎች ለጽሑፍ ፍራቻ እና ጭንቀት ይታይባቸዋል ሲሉ ይገልጻሉ። ስለሆነም በተማሪዎች ጽህፈት ውስጥ የሚፈጸሙ ስህተቶችና የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ የገመገሙ ስራዎችና የዲግሪ ማሟያ ጥናቶች በሚታዩበት ጊዜ በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ በርካታ የሆኑ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና የአረፍተ ነገርን ትክክለኛ አሰካክ ጠብቆ የመጻፍና ሀሳብን አቀናብሮ የመግለጽ ችሎታቸው አነስተኛ እንደሆነና በጥቅሉም የጽህፈት ልምምድ እድገት እያሰየ ያለመሄዱን ያመለክታሉ።

የዚህ ጥናት ትኩረት በጠምባርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች በመለየት እና በመፈተሽ የመፍትሔ ሀሳብ ለማስቀመጥ ጥረት የሚያደርግ ሲሆን በጠምባርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ስህተት ሲፈጽሙ በተለያዩ አጋጣሚዎች በመስተዋላቸው፤ የተማሪዎችን የስህተት አይነቶችን በመለየት የመፍትሔ ሀሳብ ለመስጠት ታስቦ የሚዘጋጅ ጥናት ነው።

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የተዋጣ ብቃት ይኖራቸዋል ተብሎ አይታሰብም። በመሆኑም የዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎች በሚማሩት ቋንቋ አፍ-ፈት ካለመሆናቸው የተነሳ የቋንቋውን ስርዓት ጠብቀው ያለመጻፍ ችግር በስፋት በመስተዋሉ የተማሪዎችን የስህተት አይነቶች በመለየት የመፍትሔ ሀሳብ ለማስመጥ የስህተት ትንተና ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ስለሚሆን ነው።

ስለዚህ ይህ ጥናት በጠምባርኛ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት የሚፈጽሙ ስህተቶችን መተንተን ላይ የሚያተኩር ሲሆን በአጠቃለይ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች አማርኛን

እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ በመሆናቸው የጽህፈት ክሂልን ተግባራዊ ለማድረግ ሲሞክሩ ከሚስተዋለው ስህተት መነሻነት አጥኚው በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ በጠምባሮ ልዩ ወረዳ በሙዱላ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ ሦስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የጠምባርኛ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ለመለየት ወስኗል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በመደበኛው የቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ቋንቋን የሚማሩበት ዋናው ጉዳይ በቋንቋው ውስጥ ያለውን ሰዋስዋዊ ስርዓት መለየትና መጠቀም መቻል፤ እንዲሁም አራቱን የቋንቋ ክሂሎች(ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) በማጎልበት ሀሳባቸውን በክሂሉ ተጠቅመው ለሌሎች ማስተላለፍ እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡

ተማሪዎች የቋንቋውን ክሂል ተማርን ሲሉ እውቀትን ማሳካት ብቻ ሳይሆን መቻል ያለባቸው ክሂሉን በተግባር ላይ ማዋልም ጭምር ነው፡፡ አንድ የቋንቋ ተማሪ አንድን የቋንቋ ትምህርት ከተማረ በኋላ በቋንቋው መናገር፣ ማንበብ፣ መጻፍና ማዳመጥ ይጠበቅበታል፡፡

ነገር ግን አጥኚው በሚያስተምርበት ትምህርት ቤት ውስጥ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የጽህፈት ክሂልን በሚያከናውኑበት ወቅት የተለያዩ ችግሮች ሲገጥሟቸው አስተውሏል፡፡

ለምሳሌ ያህል የድርሰት የቤት ስራዎችን፣ የድርሰት ፈተናዎችን በተለያየ ወረቀት ተሰጥቷቸው የታዩ የቃላት፣ የሀረጋት፣ የአረፍተ ነገሮች አለመጣጣም ክፍተቶች ይጠቀሳሉ፡፡

በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚገጥሟቸውን ችግሮች በጥናት መፈተሽ አስፈላጊ በመሆኑ በዚህ ርዕስ ላይ ጥናት ለማድረግ ወስኗል፡፡

ሌላው ደግሞ በጠምባሮ ልዩ ወረዳ አፋቸውን በጠምባርኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንድናቸው?

ስህተቶቹንስ የሚፈጽሙት ከምን የተነሳ ነው?

ተማሪዎቹ የአማርኛ ድርሰት እንዲጽፉ የሚታዘዙትስ በምን አይነት ስልት ነው?

የሚያስተምሩት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማስተማሪያ ዘዴ እና የማስተማሪያ መሣሪያዎች አቀራረብስ በምን አይነት ሁኔታ በክፍል ውስጥ ይተገብራሉ?

ለምሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ያለው ፍላጎት በተገለጸው ርዕስ ላይ ጥናት እንዲያደርግ አነሳስቶታል፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎቹ በቀጣዩ አመት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያጠናቅቁ እንደመሆናቸው መጠን ክሂሉን በሚገባ መተግበር ስለሚኖርባቸው የአጥኚው የትኩረት ነጥብ በድርሰት አጻጻፍ ክሂል ላይ እንዲሆን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

### 1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሙዱላ ከተማ አስተዳደርና በጠምባሮ ልዩ ወረዳ በተመረጡ ሦስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አፋቸውን በጠምባርኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች በስህተት ትንተና ዘዴዎች በመመርመር ዋና ዋና የስህተት አይነቶችን መለየት ነው።

### 1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

ከላይ ከተጠቀሰው ዋና ዓላማ በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

፡፡ በጠምባርኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን የስህተት አይነቶች መለየት፤

፡፡ በጠምባርኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን መለየት።

፡፡ ለስህተቶቹ የመፍትሔ ሐሳብ መጠቆም።

## 1.4 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ከጥናቱ ርዕስ በመነሳት ጥናቱ ለሚከተሉት መሪ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ጥረት የሚያደርግ ይሆናል።

1. በጠምባርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽህፈት ወቅት የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና ስህተቶች ምን ምን ናቸው?
2. ለነዚህ ስህተቶች መከሰት መንስኤ ይሆናሉ የተባሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
3. ለስህተቶቹ መፍትሔያቸው ምንድነው?

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

የተማሪዎችን የጽሁፍ ስህተቶች ማጥናት ተማሪዎቹ ትምህርት የሚቀስሙበትን ብልሃት መገንዘብ እንደሆነ Littlewood (1986) ይገልጻሉ።

ተማሪዎች የሚሰጣቸውን ትምህርት ይረዱ ዘንድ በጽህፈት ወቅት የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ማጥናትና መፍትሔ መፈለግ አስፈላጊ ነው። ስለዚህም ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።

፡፡ ለመምህራን የተማሪዎቹ የአማርኛ የጽህፈት ችሎታ ምን ላይ እንዳለ ጠቃሚ ፍንጭ ልሰጥ ይችላል።

፨ ከጥናቱ ውጤት በመነሳትም አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ተሻሽለው የሚዘጋጁበትን መንገድ ይጠቁማል፡፡
፨ ወደ ፊት በዚህ ርዕስ ዙሪያ ጥናታዊ ምርምር ማድረግ ለሚፈልጉ አጥኚዎች እንደ ተጨማሪ ሀሳብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በጠምባርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች እና የስህተት ምንጮችን መለየት ነው፡፡ የተማሪዎችን ስህተት በመተንተን ሂደት የሆሄያትን አሰዳደርን፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምን፣ የቃላት አጠቃቀምን፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ትክክለኛነትን እንዲሁም ከጽንሰ-ሀሳብ ግንዛቤ ጋር ተያይዞ ስህተቶችን የሚመረምር ሲሆን በአረፍተ ነገርና በአንቀጽ እንዲሁም ከዛ በላይ በሆኑ ጽሑፋዊ ይዘቶች ያለውን ስህተት በጥልቀት የጥናቱ ትኩረት አድርጎ  ጥናት ያካሄዳል፡፡ እንዲሁም በስህተት ምንጭ ትንተና ላይ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚገኙ ስህተቶች ምንጫቸው ስህተት ወይም ግድፈት መሆኑን የሚያረጋግጥ እና ሌላም መሆኑን በማረጋገጥ የመፍትሔ ሐሳብ ለመጠቆም ሞክሯል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፤ክለሳ ድርሳናት

## 2.1.ንድፈ-ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1.የስህተት ምንነት

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በጽሑፍ ሐሳባቸውን እንዲገልጹ ልምምድ ያደርጋሉ። በዚህ ልምምድ ወቅት አፋቸውን በታላሚው ቋንቋ የፈቱትም ሆኑ ኢ-አፍ ፈት የሆኑት የተለያዩ ስህተቶችን ይፈጽማሉ። ነገር ግን ስህተቶቹ ለተማሪዎቹ የቋንቋ እድገት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ እንጂ የውድቀት ምልክት እንዳልሆኑ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ (Dulay et al፣1982፣ Little wood 1984)። በተማሪዎች ጽሑፍ ውስጥ በተደጋጋሚ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ኮሌጅ የሚታዩት ስህተቶች ከመደበኛው የቋንቋ አጠቃቀም፣ በቋንቋው የጽህፈት ህግ ተቀባይነት የሌላቸውን የሆሄያት፣ የቃላት እና የአረፍተ ነገር መዋቅሮች መጠቀም እንዳልሆነ Norrish(1983፣127) ገልጸዋል። በሌላ ሁኔታ ደግሞ ስህተቶቹ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደቡ የሚችሉ መሆናቸውን ምህረት(2003)፣ Negara(1983፣35-36)ን ጠቅሰው አስቀምጠዋል። እነሱም የአጠቃቀም ስህተት እና የእውቀት ማነስ ስህተት ናቸው።

የአጠቃቀም ስህተት የሚባለው ግድፈት(Mistake) ሲሆን ይህም ዝንጋታ(laps) የሚሉት ነው። በዚህ ምክንያት የሚታየው ስህተት የተወሰኑ የቃላት ወይም የሆሄያት ግድፈት፣ ድግግሞሽ፣ የሆሄያት ጭመራ የመሳሰሉት ስህተቶች የሚታዩበት ነው። ተማሪው እነዚህን ስህተቶች የሚፈጽመው ቋንቋውን ባለማወቁ ሳይሆን በችኮላ፣ በትኩረት ማጣት፣ ባልተረጋጋ ስሜት፣ በጭንቀት ወይም በብስጭት ውስጥ ሆኖ በሚጽፍበት ጊዜ ነው።

የእውቀት ማነስ ስህተት (error) የሚባለው ግን ተማሪው በተደጋጋሚ የሚፈጽመውና በራሱ ሊያስተካክለው የማይችል፤ በሌላ ሰው እርማት /እገዛ/ እስካልተደረገለት ድረስ እንደ ትክክል የሚቆጥረው እና የሚጠቀምበት የስህተት አይነት ነው። በተጨማሪም Brown(1994፣ 205-206) ስህተትን ግድፈትና ስህተት በማለት በሁለት ከፍለው ይመለከቱታል። የተማሪዎቹን የቋንቋ ችሎታ በተገቢ ሁኔታ መተንተን ካስፈለገ በስህተትና በግድፈት መካከል ያለውን ልዩነት በሚገባ ማጤን እንደሚገባ ይገልጻሉ።

ግድፈት የሚወክለው በአፈጻጸም ችግር የሚፈጸም ስህተትን ሲሆን በይሆናል ግምትና በዝንጋታ የሚፈጠር ስህተትም በዚህ ውስጥ የሚካተት ነው።

እንደ ብራውን ገለጻ ግድፈት በማንኛውም ሰዓት የሚፈጸም አፍ-ፈትና ኢ-አፍ ፈትን የማይለይ ነው። አፍ-ፈት ተናጋሪዎች ይህን ማዳጥ ወይም ግድፈት ወዲያው ተገንዝበው ሊያስተካክሉት ይችላሉ። ስለዚህ የአፍ-ፈቶች የብቃት ማነስ ችግር ሳይሆን በአፍልቀት ሂደት የተከሰተ ክፍተት ማመልከቻ

ነው። ይህ ክፍተትም ምናልበት በጭንቀት፣ በአፍ ማዳጥ፣ በዘፈቀዳዊ የቋንቋ አጠቃቀምና በጊዜ እጥረት ምክንያት የሚከሰት ነው ይላሉ። Littlewood (1986)እና Norrish(1983) እንደሚሉት ስህተት የመማር ሂደት አንዱ አካል እና ትምህርቱንም በንቃት ለማካሄድ ጠቃሚ ምልክት ነው። ስህተት ቀደም ሲል በልማዳዊ ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች ቃለትን በማጥበቅ፣ በንቃት ባለመከታተል ወይም በእውቀት ማነስ ከትክክለኛው የቋንቋ አጠቃቀም ማፈንገጥ እንደሆነ እና በተማሪዎች ዘንድ እንደ ውድቀት የሚቆጠር፣ በመምህራኑ ችሎታ ላይም ጥያቄን የሚፈጥር እንደነበረ ይነገራል። ሆኖም ግን በሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ላይ በተካሄደ ምልካታዊ ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከታላሚው ቋንቋ ካገባብ አለማፈንገጥም ስህተት ላለመፈጸም ዋስትና ሊሆን አይችልም። በእያንዳንዱ የቋንቋ ተማሪ የሚፈጸሙ ስህተቶችም የተማሪው የቋንቋ እድገት አመልካቾች እንደሆኑ ተደርገው መቆጠር ያለባቸው ናቸው ሲሉ ገልጸዋል።

በሌላ በኩል እንደ Corder(1967፣ 156-261) አባባል የስህተት አይነቶች ግልጽ ስህተት እና ስውር ስህተት በመባል በሁለት ይከፈላሉ። ግልጽ ስህተት የሚባለው ከስሙ እንደምንረደው በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ የተፈጸመውን ስህተት አረፍተ ነገሩን በማየት ብቻ የሚንለየው የስህተት አይነት ነው። ስውር ስህተት የሚባለው ደግሞ እንደ ግልጽ ስህተት አረፍተ ነገሩን በማየት ብቻ የሚለይ ሳይሆን ስህተቱን ፈልፍሎ ለማውጣት ወይም ለማወቅ አረፍተ ነገሩን በጥልቀት እና በጥሞና መመርመርን የሚጠይቅ የስህተት አይነት ነው። በአጠቃለይ በተማሪዎች የሚፈጸሙ ስህተቶች ግድፈት ወይም ስህተት ተብለው እንደሚከፈሉ ላማወቅ ተችሏል።

## 2.2 የስህተት ትንተና ምንነት

የስህተት ትንተና ዘዴ 1967 corder በተባለ ምሁር እንደተጀመረ ድርሳናት ይገልጻሉ። ንጽጽራዊ ትንተና የጥናት ዘዴ በቋንቋ የመማር ሂደት ውስጥ የሚከተለው ስህተት ምንጩ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት አሉታዊ ሽግግር ብቻ እንደሆነ የሚገልጽ የጥናት መስክ ነበር። ይህ የጥናት ዘዴ ሌሎቹን የስህተት ምንጮች ለማጥናት ባለመቻሉ የስህተት ትንተና ይህንን አቢይ ክፍተት ለመሙላት ብሎም ለማስወገድ ብቅ ያለ የጥናት መስክ ነው። የስህተት ትንተና ማለት የተማሪዎችን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግለጽ ሲባል በበርካታ ሰዎች ዘንድ ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የሚታዩበት፣ የታዩት ስህተቶች የሚተነተኑበትና የተተነተኑትም የስህተት አይነቶች በተለያዩ ምድቦች የሚቀመጡበት ዘዴ ነው(Brown 1994፣206)። የስህተት ትንተና ስህተትን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከፋፍሎ በማጥናት የስህተት ምንጮችን ይጠቁማል። በተጨማሪም ስለ ስህተት ያለውን አሉታዊ አመለካከት በማስቀረት ስህተትን እንደ አንድ የትምህርት ሂደት ይቆጥራል። ከዚህም በመነሳት ለስርዓተ-ትምህርት ቀረጻ፣ ለማስተማሪያ መሣሪያ ዝግጅት እንዲሁም ተማሪዎች ያሉበትን የእውቀት ደረጃ ለማመልከት ያገለግላል። በአሰራሩም የቋንቋ ተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም

በናሙናነት በመውሰድ ስህተቶችን ለይቶ ያወጣል፤ የስህተቶቹንም አይነት ምንጫቸውን ምን ሊሆን እንደሚችል መላ ይመታል(corder1967፣19 እና Dulay,et al.(1982፣141-146) ገልጸዋል:: ከድክመቶቹ ውስጥ መሠረታዊ የሚባሉት ሶስቱ የሚከተሉት ናቸው::

1, በስህተት ትንተናው ሂደት ላይ ስህተቶችን እንዲህ ናቸው ብሎ በግልጽ ማስቀመጥ አለመቻል እና ምንጫቸውን በተገቢ ሁኔታ አለመግለጽ::

2, የስህተት ክፍሎችን ግልጽ በሆነ ሁኔታ አለማስፈር::

3, የተማሪዎችን ስህተቶች ቀላል በሆነ መንገድ መከፋፈል አለመቻል ናቸው::

እነዚህ ድክመቶች የተነሳበትን አላማ በተገቢው መንገድ እንደያሳካ እና ሊሰጥ የሚችለውን ጠቀሜታ እንዳይሰጥ አግደውታል::

## 2.3 የስህተት ምንጮች

ስህተቶች በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚፈጠሩ የየራሳቸውም መከሰቻ እና መንስኤ ያላቸው ክንውኖች ናቸው:: ጽህፈትም ተግባር እንደመሆኑ በዚህ ተግባር ልምምድ ላይ የሚከሰቱ ስህተቶች ይኖሩታል:: የጽህፈት ትምህርት ብዙ ልምምድን ስለሚጠይቅ በልምምድ ሂደት ከፊደላት ቅርጽ ጀምሮ እስከ ቃላት አጠቃቀም ድረስ የተለያዩ ስህተቶች ይፈጠራሉ:: አንድ ህፃን አፍ-መፍቻ ቋንቋውን ሲለምድ ሳይኮላተፍ እንደማይሳካለት ፤ሁሉ ተማሪዎችም የመጻፍን ክሂል ለመለማመድ መደናቀፋቸው አይቀርም ሲሉ Little wood(1986) ያስረዳሉ:: በተመሳሳይ Norrish(1993፣ 12-15) ስህተቶች ለትምህርት ከሚቀርቡት ነገሮች ምርጫ፣ ከትምህርቱ የአቀራረብ ቅደም ተከተል፣ በተወሰነ ቅደም ተከተል ከሚቀርበው የማስተማር ትኩረት፣ በቋንቋው ትምህርት ከሚሰጡት ምሳሌዎች፣ በምሳሌዎች አማካይነት ከሚደረገው የልምምድ ውጤት ወይም ተማሪዎቹ እነዚህን የትምህርት መረጃዎች ሲጠቀሙ ከሚኖራቸው የአጠቃቀም ሂደት ሊመጡ ይችላሉ ሲሉ ገልጸዋል:: እንደ Dulay.et.al.(1982) ማብራሪያ በቋንቋ መማር ሂደት ተማሪዎች በጽህፈት ልምምድ ጊዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምክንያት ይሆናሉ ተብለው የተገመቱ ነጥቦች በተለያዩ ምሁራን ተገልጸዋል:: ከተገለጹት ምክንያቶች ዋና ዋና ናቸው ብለው ያስቀመጧቸው፦ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ ውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች እና የማስተማር ዘዴ ድክመት እና የስነ-ልቦና ጉዳዮች ናቸው::

### 2.3.1 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ

ይህ የስህተት ምክንያት እንደ ዋነኛ ምንጭ ይቆጠር የነበረው በንጽጽራዊ የቋንቋ ጥናት አራማጆች ነበር:: በንጽጽራዊ ጥናት አራማጆች እምነት ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ዋና ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ነዉ የሚል ማጠቃለያ ነበር:: ነገር ግን ይህ ግኝት ከ1970ዎቹ አጋማሽ አላለፈም:: ተማሪዎች ስህተት የሚፈጽሙት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጣልቃ ገብነት ብቻ

አለመሆኑ የተረጋገጠው አፍ-ፈት ተማሪዎች ተመሳሳይ ስህተት ፈጽመው በመገኘታቸው ነበር::(Brown 1994):: እንደ Brown(1994፣263-264) ገለጻ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የመጀመሪያ ደረጃ መለያ ባህሪይው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሽግግር ወይም ጣልቃ ገብነት ነው። የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሽግግር ለሁሉም ተማሪዎች ዋነኛ የስህተት ምንጭ ነው። ተማሪዎች ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር ከመለማመዳቸው በፊት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሰዋስዋዊ ባህሪይ በአዕምሯቸው ተቀርጾ ይገኛል። የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው ጽህፈት ላይ በድምጽ፣ በቃላት፣ በሀረግ እና በአረፍተ ነገር አወቃቀር ውስጥ ሊታይ የሚችል ቢሆንም ስህተቱ ባይበልጥ ጎልቶ የሚታየው ግን በንበት (pronounsation) ላይ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ሁሉም ስህተቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ብቻ እንደማይከሰቱ የተለያዩ ጥናቶች አረጋግጠዋል። እንደ አጥኚዎቹ አገላለጽ በአሁኑ ወቅት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ብቸኛ የስህተት ምንጭ አይደለም። ይልቁንም ከሌሎች የስህተት ምንጮች አኳያ ሲታይ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት የሚፈጠር ስህተት እጅግ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ተገልጿል። (Ellis 1989፣ 24 Negara 1983፣ 36)። ቀድመው ከተዘረዘሩት ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው የአፍ መፍቻ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ አንዱ የስህተት ምንጭ እንጂ ዋነኛ እና ብቸኛ የስህተት ምንጭ ሊሆን እንደማይችል ነው። ስለዚህ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ በተጨማሪ ሌሎች የስህተት ምንጮች መኖራቸውን በተጓዳኝነት ያስገነዝባል።

### 2.3.2 የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ

እንደ ስህተት ትንተና አራማጆች እምነት ሌላው የስህተት ምንጭ ነው ተብሎ የተጠቀሰው አሉታዊ ውስጠ ቋንቋ ሽግግር የሚባለው ነው። ይህም ተማሪው የቋንቋውን አዲስ ስርዓት ከተማረ በኋላ ወደ አጠቃቀም ሲሄድ ውስብስብ በሆነ ውስጣዊ የቋንቋው ባህሪይ የተነሳ የሚፈጠረው ስህተት ነው። እንደ Brown(1994፣214) እና Little wood(1986፣28) ገለጻ በውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ የሚፈጠሩ ስህተቶች የምንላቸው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በሚማሩት ቋንቋ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ባህሪያት የተነሳ የሚፈጠሩ ስህተቶችን ነው። እነዚህ ስህተቶች ምንጫቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ አይደለም፤ ታላሚው ቋንቋ እንጂ። ተማሪዎቹ ለቴላሚው ቋንቋ በከፊል ከመጋለጣቸው የተነሳ ለስህተት ሊጋለጡ ይችላሉ።

ተማሪዎቹ የአንድን ቋንቋ ህግ በሚገባ ከተረዱ በኋላ ወደ አጠቃቀም ሲመጡ የተሳሳተ ማጠቃለያ በመስጠት ሊሳሰቱ ይችላሉ። እንደዚህ አይነቱ ስህተት ከህፃናት የቋንቋ ለመዳ ጋር ሊመሳሰል ይችላል። አሉታዊ የውስጠ ቋንቋ ሽግግር ወይም የተሳሰተ ማጠቃለያ ከሚያመጣቸው ስህተቶች አንዱ አንድን የቋንቋ ቅርጽ ለሁሉም በተመሳሳይ ሁኔታ ለመጠቀም መሞከር ነው። ለምሳሌ አንድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ "He went" በማለት ፋንታ "He goed" ብሎ ቢጽፍ ሁሉም የእንግሊዝኛ

ግሶች ወደ ኃላፊ ጊዜ ሲቀየሩ በቃሉ መጨረሻ "ed" ይጨምራሉ በሚል የተሳሳተ ማጠቃለያ የተፈጠረ ስህተት መሆኑን ያሳያል(Krashen1987)።

የተሳሳተ ማጠቃለያ ሲባል ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ እየለመዱ ሲመጡ የተማሩትን አዲስ ስርዓት መሰረት አድርገው በቋንቋው ለመጠቀም ሲሞክሩ የሚሳሰቱትን ማለት ነው። ይህም ቋንቋው የሚጠቀምበት መዋቅር ለሁሉም የማይሰራ ከሆነ ተማሪዎች መዋቅሩን በአጠቃለይ ለቋንቋው የሚሰራ አድርገው ሊጠቀሙበት ሲሞክሩ የሚፈጠረውን ስህተት ያሳያል። Brown(1994፣ 164-165)፣ Littlewood(1986፣23) እንዲሁም Norrish(1992፣31-32) እንደገለጹት፣ የቋንቋ ተማሪዎችን ለውስጠ ቋንቋ ስህተቶች የሚያጋልጣቸው የተሳሳተ ማጠቃለያ ብቻ አይደለም፤ያልተሟላ ትምህርት፣ የተሳሳተ ተዛምዶ እና ቃላትን ያለ አገባብ መጠቀም በውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ ለሚፈጠሩ ስህተቶች ምክንያቶች ናቸው ብለዋል። እንደ Negara(1983፣ 37-40) አገላለጽ ባልተሟላ ትምህርት የሚፈጠር ስሆተት ስንል የቋንቋ ተማሪው የቋንቋውን መዋቅር፣ ቃላት፣ የአገላለጽ ስልት ወይም ሌሎች የቋንቋውን ባህሪያት በከፍል በመማሩ የተነሳ የሚፈጠረውን ስህተት ነው። ስለዚህም ተማሪው በቋንቋ የሚገኙትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች እና ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንዲሁም ሰዋስዋዊ ስርዓቶች በከፍል በትክክል፣ በከፊል ደግሞ በስህተት ሲያፈልቁ ይስተዋላል። ለምሳሌ ያልተሟላ ሰዋስዋዊ ህግ (ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ አለመጣጣም)፣ ያልተሟላ የመስተዋድዳዊ ሀረጎች ትምህርት እና ያልተሟላ የስነ-አገባብ ብሎ መክፈል ይቻላል። ይህ ስህተት በቋንቋው ውስብስብ ባህሪይ እና የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግ በከፍል በመረዳት የሚፈጠር ስህተት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

### 2.3.3 የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት

አንድን ቋንቋ ለማስተማር የሚዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች (መጽሐፍ፣ መርሀ-ትምህርት፣ መርጃ መሳሪያዎች...)እና መምህራን የሚከተሏቸው የማስተማሪያ ዘዴዎች የስህተት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ በስህተት ትንተና ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ይገልጻሉ(Norrish 1992፣32። እና White(1980፣106-107) እንደገለጹት ልምድ ብቻውን የቋንቋ ችሎታን አያሳድግም፤ ስህተት እየተበተነ የማይታይ፣ ለስህተቱም እርማት የማይሰጥ ከሆነ የስህተቱ መጠን እየጨመረ፣ስር እየሰደደ ይመጣል። ስህተት መተርጎም አለበት ሲባል መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ስህተት ቃል በቃል እየነቀሰ በማውጣት ማረም አለበት ማለት አይደለም። ነገር ግን ተማሪው የራሱን ስህተት በራሱ ማረም የሚችልበትን ዘዴ መፍጠር ነው። ምክንያቱም ተማሪው የራሱን ስህተት በራሱ ነቅሶ ካወጣና ማስተካከያ ከሰጠ ቋንቋውን በተገቢ ሁኔታ ተገንዝቦታል ማለት ይቻላል። ስለዚህ መምህሩ የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅሞ ተማሪው የራሱን ስህተት እራሱ እንዲያርመው ቢያደርግ የመማር ማስተማር ሂደቱን ውጤታማ ያደርጋል። እንደ Norrish(1993፣2-16) በቋንቋ ማስተማር ሂደት

ውስጥ የመምህሩ የማስተማር ችሎታ ሊለካባቸው ከሚችልባቸው መስፈርቶች መካከል የቋንቋ ትምህርትን ሳቢና ማራኪ አድርጎ ማቅረብ እና የሚጠቀምባቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎች ውጤታማ ማድረግ የሚሉት ተጠቃሾች ናቸው። የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ ውጤታማ ካልሆነ ተማሪዎች ለስህተት የመጋለጥ እድላቸው የሰፋ እንደሚሆን ያስረዳሉ። እንዲሁም የቋንቋ መርሀ-ትምህርት የይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ የቋንቋን ይዘቶች ሙሉ በሙሉ ማካተት ወይም አለማካተት አንድ የቋንቋ ተማሪ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ቀላል አይደለም።

### 2.3. 4 ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች

ተማሪዎች በጽሑፍ ላይ ስህተት እንዲፈጽሙ ከሚያደርጋቸው ነገር አንዱ ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ ነው። በቋንቋ መማር ሂደት ላይ ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ ያለው በጎ አመለካከት ትምህርቱን በሚገባ እንዲከታተል የመርዳቱን ያህል፣ በቋንቋውና ቋንቋውን ተናጋሪ ማህበረሰብ ላይ ያለው አመለካከት አሉታዊ መሆን ደግሞ ለመማር ያለው ፍላጎት ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርጋል።

ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ የሚኖራቸው ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ ከቤተሰባቸው፣ ከአካባቢያቸው፣ ከጓደኞቻቸውና ከተለያዩ ተላውጦዎች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያለው ነው። በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ለሚጽፉት ፅሑፍ ያላቸው ትኩረት ይቀንሳል፤ ስህተቱ በአንጻሩ ይጨምራል(Norrish 1992፣18)። ስነ-ልቦናዊ ጉዳይ ሲባል የሚያያዘው ከተማሪዎቹ የግል ጉዳዮች ጋር ሲሆን፤ ተማሪዎቹ ከክፍል ውጪ ስላለው ሁኔታ በአዕምሯቸው ውስጥ ይዘውት የሚመጡት ነገር በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በሚገባ እንዳይከታተሉ ስለሚያደርጋቸው ነው(Norrish 1992፣19)።

Dubin እና Olshtain(1986፣15) እንደጻፉት ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ላይ አሉታዊ አተያይን ከሚፈጥሩ ምክንያቶች አንዱ ከቋንቋው ከሚገኘው ጥቅም ጋር የተገናኘ ነው። በመሆኑም ተማሪው ከቋንቋ ትምህርቱ ጥቅም አገኝበታለሁ ብሎ ካሰበ ለቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት በማዳበር ቋንቋውን ለመማር ያለው ፍላጎት ይጨምራል፤ በዚህም የተነሳ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ውስጥ የሚፈጽማቸው ስህተቶች ይቀንሳሉ። በአንጻሩ ተማሪው ቋንቋውን ከተማረ በኋላ ምንም አይነት ተጨባጭ የሆነ ጥቅም እንደማያገኝ ከተገነዘበ ለቋንቋው ያለው አመለካከት ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፤ በጽሁፍ ውስጥ የሚፈጽማቸው ስህተቶችም ሊጨምሩ ይችላሉ።

በአጠቃለይ ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ አሉታዊ አተያይ ካለው ወጥነትና ተከታታይነት ያለው የቋንቋ አጠቃቀም ከሌለው፣ ከቋንቋው ማህበረሰብ ባህል እና ልማድ የሚጋጭ ከሆነ ወይም ለመማር ውስጣዊ ተነሳሽነት ከሌለው በጽሑፉ እና በንግግሩ ውስጥ ስህተቶች እየጨመሩ መሄዳቸውን መረዳት ይቻላል።

### 2.3.5. የመጻፍ ክሂል ያለበት ደረጃ

በኢትዮጵያ በ1944 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በተቀረጸው የአንደኛ ደረጃ ስርዓተ-ትምህርት ውስጥ አማርኛ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ተካቶ እናገኛለን። ይህ ስርዓተ-ትምህርት በ1951 ዓ.ም ተሻሽሎ ሲወጣ የትምህርት አይነቶች በውስጣቸው ሊይዟቸው የሚገቡ ይዘቶችን አካቶ ነበር።በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች አንዱ ደግሞ የድርሰት አጻጻፍ ነበር።(የትምህርት ሚኒስቴር1970) አማርኛ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርትነት ከሚሰጥባቸው አጠቃለይ አላማዎች አንዱ ተማሪው የቋንቋውን ስርዓት ጠብቆ ሀሳቡን በጽሑፍ መግለጽ ማስቻል እንደሆነ ተስፋዬ(1981፣59) ገልጸዋል። ይሁን እንጂ የመጻፍን ክሂል ማስተማር በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ልምድ ቢኖርም እስካሁን የታለመለት ግብ በሚጠበቀው መጠን ተሳክቶ አይታይም። ለዚህም የሀገራችን የዘርፉ አጥኚዎች አሉታዊ አስተያየቶችን ሲሰነዝሩ ይታያል። የመጻፍ ክሂል በተማሪዎች ዘንድ እስከ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ በጣም አስቸጋሪ እና ከስህተት ያልጸዳ መሆኑን ባየ(1987)፣ ተስፋዬ(1981) ገልጸዋል።

ሆኖም ይህ ችግር በኢትዮጵያ ብቻ የሚታይ አለመሆኑን የሚያረጋግጡ የተለያዩ የውጭ ሀገር የቋንቋ ምሁራን በጽሑፎቻቸው ያስነብባሉ። ይህንኑ ሀሳብ አስመልክቶ Rechards (1974፣100) "በዩኒቨርሲቲ ደረጃ እንኳን ብዙዎቹ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ በተማሩት መሠረት ጥሩ ጽሑፍ ሲጽፉ አይታይም" ሲሉ ይገልጻ

## 2. 4. መጻፍ ለምን አስቸጋሪይሆናል?

መጻፍ የሀሳብ አቀነባበርን፣ የሀሳብ ፍሰትን፣ የቃላት አመራረጥን እና የአገላለጽ ስልትን የሚጠይቅ የቋንቋ ክሂል ነው። ስለዚህ ብዙዎች እንደሚስማሙበት መጻፍ የነቃ አዕምሮ ወጤት ነው ማለት ይቻላል። ሆኖም ግን የመጻፍ ክሂል በብዙዎች ዘንድ አስቸጋሪ መሆኑ ይገለጻል። መጻፍ ለብዙዎች አስቸጋሪ የሚሆንበትን ምክንያት Byrne(1988) ሲያስረዱ ሶስት ምክንያቶችን ይጠቅሳሉ፤ እነሱም፦ ስነ-ልቦናዊ ችግር፣ ሰዋስዋዊ ችግር እና ግንዛቤያዊ ችግሮች ናቸው።

### 2.4.1 ስነ-ልቦናዊ ችግር

መጻፍ ከንግግር የበለጠ ስነ ልቦናዊ ጫና ያሳድራል። Byrne(1997፣4) እንደሚያስረዱት ንግግር ተፈጥሯዊ፣ በየትኛውም ቦታና ሁኔታ ውስጥ ስንናገር ስህተት ብነፈጽም ከአድማጭ እርማት እናገኛለን፤ ሀሳባችንን በጽሑፍ ስንገልጽ ግን ያለ ማንም እገዛና ያለምንም ማስተካከያ በራሳችን

የሚንወጠው ተግባር ይሆናል። ይህ ደግሞ የስነ-ልቦና ጫና ስለሚያሳድር መጻፍን አስቸጋሪ ያደርገዋል።

## 2.4.2 ሰዋስዋዊ ችግር

እንደ Byrne(1997፣4-5) ገለጻ በንግግር ወቅት ገለጻ ስናደርግ አድማጭ ንግግራችን እንዲቀጥል ያግዘናል። ንግግራችን ላይ ስህተት ቢፈጠር እየደገምን ወደ ኋላ እየተመለስን አስተካክለን መጠቀም እንችላለን። በጽህፈት ጊዜ ግን እነዚህ ሁሉ እድሎች አይኖሩም። ተግባቦታችን በራሳችን ችሎታና እውቀት ብቻ የተገደበ ይሆናል። በራሳችን የቃላት ምርጫ፣ በራሳችን የቃላት መዋቅር አረፍተ ነገሮችን መመስረት ይጠበቅብናል። ከዚህ ሂደት በኋላ የጻፍነው ጽሑፍ በአንባቢ ይተረጎማል። የጽህፈት ተግባር የተለያዩ የቋንቋ ህግጋትን ማሰላሰልን የሚጠይቅ ሲሆን የጽሕፈት ክሂልን ተግባራዊ ስናደርግ የሰዋስው እውቀት አስፈላጊ ነው። የተለያዩ የስነ-ልሳን ዘርፎች በተለያዩ ስልቶች የቋንቋውን አጠቃለይ መልክ ያጠናሉ። በመሆኑም ጽሕፈትና ስነ-ልሳን ተሐያይተው ሊታዩ አይገባም። የጽህፈት ጥናት ከቋንቋው ስርአት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከጽሕፈት ጋር አብሮ እንዲጠና ሁኔታዎች ያስገድዳሉ። በመሆኑም የተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ለመፈተሽ የቋንቋውን ስርአት አብሮ ማየት ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ ሌላው የጽሕፈትን ተግባር አስቸጋሪ የሚያደርገው ነገር ነው።

## 2.4.3 የግንዛቤ ችግር

ንግግር መልዕክት ለማስተላለፍ ያለ ማንም ጋባዥ፣ ያለ ማንም አስገዳጅነት፣ በራሳችን ፍላጎትና ባሸን ጊዜ የሚንጠቀመው መግባቢያ ነው። የቋንቋውን የጽሕፈት ህግ በሚገባ ማወቅ ይጠይቃል። የቋንቋው የጽህፈት ህግ ብቻ ሳይሆን ሀሳባችንን በጽሑፍ እንዴት መግለጽ እንዳለብንና ከአንባቢያችን ጋር ያለምንም ችግር እንዴት መግባባት እንደምንችል ማወቅ ይኖርብናል። ይህም ሦስተኛው የመጻፍን ክሂል አስቸጋሪ የሚያደርገው ሂደት ነው በማለት Byrne(1997፣5) አብራርተዋል። ሆኖም በላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ተማሪዎች በጽሑፋቸው ውስጥ የተለያዩ ስህተቶችን ይፈጽማሉ።

## 2.5 የስህተት ትንተና ማካሄድ ጠቀሜታ

ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት መከሰትም ሆነ አለመከሰት የስህተት ትንተና የሚሰጠው ጠቀሜታ በጣም ከፍተኛ ነው። እንዲሁም በተማሪዎች ድርሰት ላይ የስህተት ትንተና ማከሄድ በርካታ ስነ-ትምህርታዊ ፋይዳዎች እንዳሉት ምሁራን ይገልጻሉ። የስህተት ትንተና ማከሄድ ታላሚውን ቋንቋ በመማር ማስተማሩ ሂደት እንደ አቅጣጫ ጠቋሚ መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ይህንን ሀሳብ Loft(1983፣256) የስህተት ትንተና ለመምህራን የተማሪዎቻቸውን ስህተቶች እንዴት መተንተን እንደሚችሉ ቴክኒኮችን በማቅረብ በኩል ጠቀሜታ ያለው ስራ እንደሆነ ይገልጻሉ። ሌላው የስህተት ትንተና ከዚህ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች እንደሚያስገኝ Loft(1983፣ 256) እና Sharma(1979፣ 76-77) ገልፀዋል። ጠቀሜታዎቹም ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ ያላቸው እውቀት ምን ያህል

እንደሆነና ጠንክረው ቢሰሩ የትኞቹን ስህተቶች በቀላሉ እንደሚያስወግዱ፤ እንደዚሁም የትኛው የታላሚው ቋንቋ ክፍል ላይ ትኩረት ሰጥተው መለማመድ እንዳለባቸው ሊጠቁም ይችላል:: በአንድ ክፍል ውስጥ በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ቢኖሩ የጋራ ስህተታቸው የትኛው እንደሆነ፤ በአንዱ ቋንቋ አፉን የፈታ ተማሪ ከሌሎቹ የተለየ የሚፈጽመው ስህተት ካለ የትኛው አይነት ስህተት እንደሚፈጸም እና የስህተትቱ ምንጭ ምን እንደሆነ ለመረዳት ይጠቅማል::
የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በእድሜና በክፍል ደረጃቸው መጠን የሚሰሩት ስህተትም ይለያያል:: ይህንንም ለመረዳት የስህተት ትንተና ያስፈልጋል:: በስህተት ትንተና ተማሪዎች የትኞቹን የታላሚ ቋንቋ ክፍሎች እንደምሳሰቱ ለማወቅ ይቻላል:: በተወሰነ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ከሌሎች ተለይተው ስህተት የሚፈጽሙባቸው የቋንቋ ክፍሎች አሉ:: ስህተቶቹ ስነ-ድምጻዊ፣ ስነ-ምዕላዳዊ፣ ስነ-አገባባዊ ናቸው? ወይስ ሌላ? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል:: የስህተት ትንተና የቋንቋ ትምህርቱ ከቀረበ በኋላ ብቻ የሚከናወን ጉዳይ አይደለም:: ይህንን ሀሳብ Sharma(1979፣77) ሲያብራሩ የቋንቋ መምህር ትምህርቱን ከመጀመሩ በፊት፣ የመማር ማስተማሩ ሂደት እየተካሄደ አሊያም ከቋንቋ ትምህርቱ በኋላ የስህተት ትንተና በማካሄድ የትምህርቱን አቀራረብ ሊገመግም፣ ማሻሸያ ሊያደርግና የመፍትሔ ሀሳብ ሊያፈላልግ ይችላል::
የስህተት ትንተና ለመምህሩ የሚሰጠው ጥቅም ቀላል እንዳልሆነ Corder(1974፣25) ሲገልጹ ለመምህሩ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ችግሩ ጎልቶ የሚታይባቸውን የቋንቋ ይዘቶችን አውቆ ለመለየትና ከስህተቶቹ በመነሳት ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችለውን ዘዴ በመቀየስ የመፍትሔ ሀሳብ ለማፈላለግና ለማስተማሪያነት የሚጠቀምበትን የማስተማሪያ መሳሪያዎች ውጤታማነትና ብቃት ለማረጋገጥ ስለሚረዳ መምህሩ ከስህተት ትንተና የሚያገኘው ጥቅም በትንሹ የሚገመት አይደለም:: የስህተት ትንተና ለመምህሩ ከሚኖረው ፋይዳ በተጨማሪ ለቋንቋ ተማሪዎችና ለመርሀ-ትምህርት አዘጋጆች ከፍተኛ ጥቅም እንደሚሰጥ Lengo(1995፣20-21) ገልጸዋል:: ለቋንቋ ተመራማሪዎች አንድን ቋንቋ እንዴት መማር እንደሚቻልና ተማሪው ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት የሚጠቀምባቸውን ብልሃቶችንና ቅደም ተከተሎችን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ይጠቅማል:: በመርሀ-ትምህርት ቀረጻ ላይ ለተሰማሩ ባለሙያዎች እና ለማስተማሪያ መሣሪያ አዘጋጆች መረጃ በመስጠት በመርሀ-ትምህርትና ማስተማሪያ መሣሪያዎች ውስጥ ለየትኞቹ ይዘቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው መደራጀት እንዳለባቸው መረጃ ይሰጣል::
የስህተት ትንተና ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት በመሆኑ በተማሪዎች የተለያዩ ቋንቋ የመማር ሂደት ላይ ትንተና ማካሄድ በእጅጉ ይጠቅማል:: ከላይ ከተገለጹት ነጥቦች በተጨማሪ በአንድ የትምህርት መርሀ-ግብር  መነሻ፣ መካከልና መድረሻ የስህተት ትንተና ማድረግ ጠቃሚነቱ የጎላ ነው::

በትምህርት መነሻ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ያላቸውን ዳራዊ እውቀት ለመረዳት በትምህርት ማዕከል የትምህርቱ ሂደት ምን ያህል በተገቢ ሁኔታ እየሄደ እንደሆነ በመገምገም በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት ያገኙትን እውቀት እና የቀረፏቸውን ስህተቶች ለመገንዘብ ይጠቅማል፡፡ መምህራን በትምህርት መርሀ-ግብሩ ሂደት የማስተማሪያ ዘዴያቸው ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ እና የትኞቹን ተማሪዎች በምን አይነት መንገድ መርዳት እንደሚችሉ የስህተት ትንተናው ሊጠቁማቸው ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ምርምር ሊደረግባቸው የሚገቡ ነጥቦችንም ይጠቁማል፡፡

## 2.6 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል ውስጥ ከዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ያላቸው ስራዎች የተቃኙበት ክፍል ነው፡፡

የመጀመሪያው ጥናት፦ ምህረት (1998) በሀድይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች አጥንተዋል፡፡ በውጤቱም የስህተት አይነቶቹ፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተቶች እና ለመለየት ያልተቻሉ የስህተት አይነቶች መሆናቸው ተጠቅሷል፡፡ ለስህተቶቹም መከሰት ምክንያት ያደረጉት በውስጠ ቋንቋ፣ በመማር ማስተማር ሂደት፣ በስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች እና በሌሎች ተጽእኖዎች የተፈጸሙ መሆናቸው ተገልጿል፡፡

ሌላው ወርቁ(2009) "አፋቸውን በመጀንግረኛ ቋንቋ የፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማሪኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዳለች፡፡ የስህተት ምንጮቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የታላሚው ቋንቋ እና የማስተማሪያ መሣሪያዎች ተጽእኖዎች መሆናቸው ተገልጿል፡፡

ልዑል ሰገድ(1997) በወላይትኛና በሲዳምኛ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ ስህተቶችን የጠኑ ሲሆን ትኩረት ያደረጉትም ስነ-ልሰናዊ ስህተቶች ላይ ነው፡፡ ይህንንም በአራት ክፍሎች ዳስሰዋል፡፡ እነዚህም በድምጽ ደረጃ፣ በቃላት ደረጃ፣ በሀረግ ደረጃ እና በአረፍተ ነገር ደረጃ የተፈጸሙ ስህተቶች የሚሉ ናቸው፡፡ ለስህተቶቹ መፈጠር በምክንያትነት የተዘረዘሩት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴ ድክመት እንዲሁም ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ህይወት(2009) "በወላይተኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህቶትች ትናተና" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዳለች፡፡ የዚህ ጥናት ውጤት የሚያመለክተው  ችግሮቹ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች፣ የቋንቋ አወቃቀር (የሰዋስው) ስህተቶች፣

የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች እና ከጽንሰ-ሀሳብ ጋር የተያያዙ ስህተቶች ናቸው። የስህተቶቹ ምንጮች የውስጠቋንቋ ተጽዕኖ እና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖዎች መሆናቸው ተገልጿል።

ሀብታሙ(2009) በሸናሸኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል። የስህተቶቹን አይነትና ምክንያት ሲገልጹ ስህተቶቹ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም፣ የጽንሰ-ሀሳብ ግንዛቤ እና መለየት ያልተቻሉ ሲሆኑ ምክንያቶቹ የውስጠቋንቋ ተጽእኖ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት መሆናቸው ተገልጿል።

ተገኝ(2000)"አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል። በጥናቱ ግኝት መሠረት ስህተቶቹ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርአተ-ነጥብ አጠቃቀም፣ የጽንሰ-ሀሳብ ግንዛቤ እና መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች ሲሆኑ፤ የስህተቶቹ ምንጭ ደግሞ በውስጠ ቋንቋ፣ በመማር ማስተማር ሂደትና በመማሪያ መሣሪያዎች እንዲሁም በስነ-ልቦናዊ ማህበራዊ ሁኔታ መሆኑ ተገልጿል።

አልማዝ(2011) "በከምባትኛ አፍ-ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና በሺንሺቾ ከተማ አስተዳደርና በቃጫብራ ወረዳ በተመረጡ አራት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዳለች። በጥናቱ ግኝት መሠረት የስህተት ምንጮች ተብለው የተቀመጡት ውስጠ-ቋንቋ ተጽእኖ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የመማር ማስተማር ሂደትና የስነ-ልቦናዊ ተጽእኖ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ጥናታዊ ጽሑፎች በተለያየ ሀገርኛ ቋንቋ አፋቸውን ፈትተው በአማርኛ ጽህፈታቸው ላይ የተለያዩ ስህተቶች በተገኙባቸው ተማሪዎች ላይ የተደረጉ ፍተሻዎች ናቸው። የተገኘውን የጥናት ውጤት ስንመለከት ሁሉም ጥናቶች ለስህተት ምንጭ ይሆናሉ ያሏቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል።

በልኡል(1997) የጥናት ውጤት መሠረት አረቱም የስህተት ምንጮች ለተጠኚ ተማሪዎች የጽሑፍ ስህተት ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ ተገልጿል።

በአንጻሩም በህይወት (2009) የጥናት ውጤት መሠረት ለስህተት ምክንያት ይሆናሉ የተባሉት የውስጠቋንቋ ተጽእኖ እና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖዎች ናቸው።

ሀብታሙ(2007) በጥናታቸው ውጤት ለተጠኚ ተማሪዎቹ ስህተቶች ምክንያት ሆነው ያገኟቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ የመማር ማስተማር እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ዝግጅት ድክመትን ነው።

በተገኝ(2000) የጥናት ውጤት መሠረት ለስህተቶቹ ምክንያት የሆኑት የስነ-ልቦና ጫና፣ የመማር ማስተማር እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ዝግጅት ድክመት እንዲሁም የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ መሆናቸው ተገልጿል።

ምህረት(1998) በጥናታቸው ውጤት መሠረት ለስህተቶቹ መከሰት ምክንያት የሆኑት በውስጠ ቋንቋ፣ በመማር ማስተማር ሂደት፣ በስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች እና በሌሎች ተጽእኖች የተፈጸሙ መሆናቸው ተገልጿል።

ወርቁ(2009) በጥናቷ ውጤት መሠረት የስህተት ምንጮቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የታላሚው ቋንቋ እና የማስተማሪያ መሣሪያዎች ተጽእኖዎች መሆናቸው ተገልጿል።

አልማዝ(2011) በጥናቷ ውጤት መሰረት የስህተት ምንጮቹ የውስጠ-ቋንቋ ተጽእኖ፣ የአፍ-መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የመማር ማስተማር ሂደትና የስነ-ልቦናዊ ተጽእኖ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ስራዎች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ላይ መካሄዳቸው እና የስህተት ትንተና ጥናት ላይ ያተኮሩ መሆናቸው ነው። በአንጻሩም ይህ ጥናት ከላይ ከተዘረዘሩ ስራዎች የሚለየው በጠምባርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት የሚፈጽሟቸው  ስህተቶች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ነው።

# ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

## 3.1 የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የጠምባርኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሑፋቸው ላይ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ይፈትሻል፡፡ ለዚህም የተመረጠው የአጠናን ዘዴ አይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴን የሚከተል ይሆናል፡፡ ይህም የምርምር ዘዴ የተመረጠበት ዋናው ምክንያት የሚሰበሰበውን መረጃ ፈትሾ የጥናቱን ውጤት ትረካንና ገለጻን በመጠቀም መረጀዎችን ለመተንተንና አብራርቶ ለማቅረብ ስለሚያስችል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መጠናዊ የምርምር ዘዴ የሚተገበርበት ምክንያት ደግሞ ከድርሰት የሚሰበሰበው መረጃ የስህተቶች ብዛት በቁጥር ተጠናቅሮ በመጠን የሚገለጽ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚፈለጉ ተጠኚዎች በሚከተሉት የናሙና አመራረጥ ስልት ይመረጣሉ፡፡

## 3.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ በጠምባሮ ልዩ ወረዳ ከሚገኙ አምስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በሦስቱ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ እነዚህም ትምህርት ቤቶች ሙዱላ ከፍተኛ ሁለተኛና መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ ቀለጣ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ሆዶ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቶቹ የተመረጡት በአመቺ ናሙና ስልት ነው፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ካለው የገንዘብ መጠን፣ የጊዜ ጉዳይና የቦታ ርቀት ጋር በማጣጣም እና በልዩ ወረዳው ውስጥ ከሚገኙ ከተለያዩ ቀበሌያት የሚመጡ ተማሪዎችን በአንድ አካባቢ በቀላሉ ማግኘት ስለሚቻል ነው፡፡

## 3.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው የክፍል ደረጃ 9ኛ ክፍል ነው፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ተተኳሪዎች አፋቸውን በጠምባርኛ የፈቱ ተማሪዎችና የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡ የክፍል ደረጃውም የተመረጠው በአላማ ተኮር ናሙና ዘዴ ነው፡፡ የተመረጡበትም ምክንያት በዚህ የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በቂ ጊዜ ስለሚኖራቸውና መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ተብሎ በመገመቱ ክፍሉ ሊመረጥ ችሏል፡፡ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ከሚኖረን የጊዜ ውስንነት አንፃር በጥናቱ አልተካተቱም፡፡

## 3.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የዘጠነኛ ክፍልን አማርኛ በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራን ---6--- ብቻ በመሆናቸው በጠቅላይ ናሙና ዘዴ በመጠቀም ሁሉም በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል።

## 3.5 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የሚያተኩረው በጠምባርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ላይ በመሆኑ በቅድሚያበእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በጠምባርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ይለያሉ። በሙዱላ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ በ2016 ዓ/ም በ9ኛ ክፍል በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በድምር 200 ሲሆኑ የሚፈለገው ተማሪ ብዛት 34 ነው፤ ስለዚህ 200÷34=5.8 ይሆናል። በዚህ ውጤት መሠረት በየስም ዝርዝራቸው በየአምስት ተማሪ ርቀት(interval) ተማሪዎች ተመርጠዋል። በዚህም መሠረት በሦስቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ በጠምባርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ቁጥር 342 ሲሆኑ ከነዚህም ተማሪዎች መካከል ድርሰቱን ለመጻፍ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት 34 ተማሪዎች የተወሰዱ ሲሆን በድምሩ 102 ተማሪዎች ለጥናቱ ተመርጠዋል።ይህ የተደረገው በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ያሉት ጠምባርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች ድምር ለተጠኝ ተማሪዎች ቁጥር በማካፈል በሚገኘው ውጤት አንጻር ከጥናቱ አካላይ የስም ዝርዝር በተወሰነ የረድፍ ርቀት ላይ የሚገኙትን ስሞች በመውሰድ ነው።

## 3.6 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱ አመቺና አስፈላጊ የሆኑና የጥናቱን አላማ ያሳካሉ ተብለው የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ድርሰትን ማጻፍ እና የጽሑፍ መጠይ ናቸው።

### 3.6.1 ድርሰት ማፃፍ

ለጥናቱ ይጠቅማሉ ተብለው ከታሰቡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ዋነኛው የድርሰት ፈተና ነው። የድርሰት ፈተናው እንዲጻፍ ከመቅረቡ በፊት የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ እድሜ እና ልምድ ባገናዘበ መልኩ አስራ አንድ ርዕሶች ተዘጋጅተው በአማካሪ ተገምግመው አስተያየት ከተሰጠባቸው በኋላ ለተማሪዎች ቀርበዋል።

የድርሰት ፈተናዎቹ ነጻ የድርሰት አጻጻፍ ስልትን በመከተል የሚጻፉ ሲሆን የመጀመሪያ ዙር የድርሰት መልመጃ ያለ ምንም ቅድመ ዝግጅት ክፍል ውስጥ እንዲጽፉ ከተደረገ በኋላ የሁለተኛው ዙር ድርሰት መልመጃ ደግሞ ከሳምንት በኋላ በአማራጭ ከሚቀርቡላቸው ርዕሶች መካከል በመረጡት ርዕስ ላይ ብቻ ተዘጋጅተው በመማሪያ ክፍል ውስጥ እንዲጽፉ ተደርጓል።

### 3.6.2 መጠይቅ

#### 3.6.2.1. የመምህራን መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዓላማው መምህራን ጽህፈትን በተመለከተ ስለተማሪዎች ዳራ፣ መርሀ-ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፉ የጽህፈት ክሂልን ለማዳበር ስላላቸው ጠቀሜታ፣ ስለመማር ማስተማሩ ሂደት፣ ተማሪዎች ለቋንቋው ስለሚኖራቸው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አመለካከት፣ በአጠቃለይ ስለ ስህተት አይነቶች መምህራን ያላቸውን አስተያየት ለማግኘት ነው። የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ በአማካሪ ከተገመገመ በኋላ ለመምህራኑ ቀርቧል።

መጠይቁ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጠይቁ የመጀመሪያ ገጽ ላይ የመጠይቁ ዓላማ ተብራርቷል።

ክፍል አንድ የመምህራኑን አጠቃለይ ማንነት በተመለከተ መረጃ ለማግኘት የተዘጋጀ ነው። በክፍል ሁለት ስለመማር ማስተማር ሂደትን የተመለከቱ ጥያቄዎችና የተማሪዎቹን የስህተት አይነቶች አስመልክቶ የሚጻፉ ነገሮች ያሏቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። በአጠቃላይ በመምህራን ግንዛቤና ከማስተማር ልምድ አንጻር የሚመለሱ 12 ክፍት ጥያቄዎች ለመምህራን ቀርበዋል።

## 3.7 የመረጃ አተናተን

ለዚህ ጥናት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች ከድርሰቶች እና ከጽሑፍ መጠይቆች ተሰብስበው ተዘጋጅቷል። የተገኙትን መረጃዎች በምሳሌ በማስደገፍ በሰንጠረዥ በትንተና እና በገለጻ መልክ ቀርቧል።

### 3.7.1 የመጠይቆች አተናተን

በዚህ ጥናት በአማርኛ መምህራን የሚሞሉት መጠይቆች ተማሪዎቹ ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የስህተት ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡ ነገሮችን ይጠቁማሉ።

መረጃዎቹ ገላጭ የአተናተን ዘዴን በመጠቀም በጭብጥ ተመሳስሎነት ተተንትኗል።

### 3.7.2 የድርሰት ፈተና አተናተን

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ለማደራጀት እና ለመተንተን በቅድሚያ ለጥናቱ የተመረጡ ተማሪዎች ድርሰት እንዲጽፉ ተደርጓል። ተማሪዎቹ ድርሰቱን ለመጻፍ በአጥኚው የተዘጋጁ እና በአማካሪ የተገመገሙ፣ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ መሰረት ያደረጉ አስራ አንድ ርዕሶች ቀርበዋል። ተማሪዎቹ ከቀረቡት ርዕሶች ውስጥ ሁለት ርዕሶች መርጠው የመጀመሪያ ዙር የድርሰት መልመጃ ያለ ምንም ቅድመ ዝግጅት ክፍል ውስጥ እንዲጽፉ ከተደረገ በኋላ፣ የሁለተኛውን ዙር ድርሰት ደግሞ ከሳምንት በኋላ በአማራጭ ከቀረቡላቸው ርዕሶች መካከል በመረጡት ርዕስ ላይ ብቻ ተዘጋጅተው በመማሪያ ክፍል ውስጥ እንዲጽፉ ተደርጓል። ድርሰቶቹ ሰባት

በተለያየ ቅጂ ተባዝተው በሶስቱም ትምህርት ቤት ባሉ የአማርኛ መምህራን ታርመዋል። የአስተራረም ሂደቱ፦ አራሚዎቹ በድርሰቱ ውስጥ ሊያገኟቸው የሚችሉትን ስህተቶች በአጥኚው በተዘጋጁ የቅድመ ምደባ መስፈርቶች እንዲመድቧቸው ተደርጓል። እነዚህ የምደባ መስፈርቶች የተዘጋጁት አጥኝው አስቀድሞ ድርሰቶቹን በማረም ከሚያገኛቸው ስህተቶች በመነሳት ነው። ለስህተቶቹ ምደባ የተዘጋጁት ምድቦች የስርዓተ ነጥብ ስህተት፣ የቃላት ወይም የሆሄያት ግድፈት፣ ጭመራ ወይም የቃላት ድግግሞሽ፣ የሆሄያት ቅርጽ፣ የጽንሰሀሳብ ግንዛቤ ስህተት፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የኢ-መደበኛ ቃላትና ሀረጋት፣ የሰዋስው ስህተት(የመደብ፣ የጾታ እና የቁጥር ስምምነት) ወዘተ ናቸው። በዚህ መለኪያ መሰረት መምህራኑ ያገኟቸውን ስህተቶች ብዛት እና አይነት እንዲመድቧቸው ተደርጓል።

በዚህ መልኩ ታርመው የተከፋፈሉትን ስህተቶች በማመሳከር የጋራ የሆኑት ተወስደው ለጥናቱ በሚመች መልኩ ተደራጅተው ተተንትነዋል። ስህተቶቹን በአይነት በአይነት ለመመደብ፤ ስህተቶቹንም ለመቁጠር እና የስህተት ትንተና ለማድረግ የሚጠቅሙ ሁለት አባይት ዘዴዎች አሉ። እነሱም፦ ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የአከፋፈል ዘዴ እና ስህተትን መሰረት ያደረገ የአከፋፈል ዘዴ ናቸው(Norrish1983፣81-89)።

ከነዚህ ዘዴዎች ውስጥ በዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ የዋለው ቅድመ ግንዛቤን መሠረት በደረገ ምድብ ውስጥ የተማሪዎችን ስህተት መመደብ ነው። ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በመጠኑም ቢሆን አሻሚ የሆነውን የአከፋፈል ዘዴ የሚያቃልል እና ለአከፋፈል የሚያመች በመሆኑ ነው። በዚህ መሠረት ስህተቶቹን ለመተንተን የሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ተከናውነዋል። ስህተቶቹን በአይነት ለመመደብ፣ ለመቁጠርና ድግግሞሻቸውን ለማወቅ የNorrish(1983፣103-104) የስህተት አተናተን ስልት እንደሚከተለው ተግባራዊ ተደርጓል።

1. ድርሰቶቹ የተጻፉበት የቃላት ብዛት እንዲደመር ተደርጓል። በእያንዳንዱ ድርሰት ውስጥ የሚገኙ ስህተቶች ተደምረዋል።

2. ስህተቶቹ አስቀድሞ በተመደበላቸው ምድብ እንዲቀመጡ ከተደረገ በኋላ በእያንዳንዱ የስህተት አይነት የተፈጸሙ የስተቶች ብዛት ታውቋል።

3. ድርሰቶቹ የተጻፉበትን ቃላት መጠን ለድርሰቶቹ ቁጥር በማካፈል በአንድ ድርሰት ውስጥ የሚገኘው አማካይ የቃላት ብዛት ታውቋል።

4. የስህተቶቹን መጠን ለድርሰቶቹ በማካፈል በአማካይ በአንድ ድርሰት ውስጥ ምን ያህል ስህተቶች እንደሚገኙ ታውቋል።

5. አጠቃለይ የቃላቱን ብዛት ለአጠቃለይ የስህተት ብዛት በማካፈል አንድ ስህተት በምን ያህል ቃላት ውስጥ እንደሚገኝ ተለይቷል።

6. የስህተቶቹን መጠን በመቶ በማባዛት እና የተገኘውን ውጤት ድርሰቶቹ በተጻፉበት የቃላት ብዛት በማካፈል በመቶ ቃላት ምን ያህል የስህተት ድግግሞሽ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል።

የስህተት አተናተን ቀመር (Formula) የሚከተለውን ይመስላል፡-

$$\text{የአንድ ድርሰት አማካይ የቃላት ብዛት} = \frac{\text{የቃላት ብዛት}}{\text{ለድርሰት ብዛት}}$$

ይህ ማለት በአንድ ድርሰት ውስጥ በአማካይ ምን ያህል ቃላት እንዳሉ የሚገልጽ ነው።

$$\text{አማካይ ስህተት} = \frac{\text{አጠቃላይ የስህተት ብዛት}}{\text{አጠቃላይ የድርሰት ብዛት}}$$

ይህ የሚገልጸው በአንድ ድርሰት ውስጥ በአማካይ ምን ያህል ስህተቶች እንዳሉ ነው።

$$\text{የስህተት ድግግሞሽ} = \frac{\text{አማካይ ስህተት} \times 100}{\text{አማካይ ቃላት}}$$

ይህ የሚገልጸው በአንድ መቶ ቃል ውስጥ አንድ ስህተት ምን ያህል ጊዜ እንደሚደጋገም ነው።

$$\text{የትክክለኛነት ተዛማጅነት} = \frac{\text{አጠቃላይ የቃላት ብዛት}}{\text{አጠቃላይ የስህተት ብዛት}}$$

ይህ ስሌት የሚያመለክተው አንድ ስህተት በምን ያህል የቃላት ብዛት ውስጥ እንደሚገኝ የሚገልጽ ነው።

## 3.5.2 የመጠይቆች አተናተን

Dulay et,al.(1982,140-146) እንደገለጹት ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው የተለያዩ ስህተቶች ምክንያታቸው ምን እንደሆነ እርግጠኛ ሆኖ መናገር አስቸጋሪ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት በተጠኚ ተማሪዎች እና በአማርኛ መምህራን የተሞሉት መጠይቆች ተማሪዎቹ ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የስህተት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ነገሮችን ይጠቁማሉ። መረጃዎቹ ገላጭ የአተናተን ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል።

# ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተና

## 4.1 በድርሰቶቹ ውስጥ የታዩ አጠቃላይ የስህተት ብዛት

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዚህ ንዑስ ክፍል በድርሰቶቹ ውስጥ የተገኙት ስህተቶች ከነሙሉ መረጃቸው በዝርዝር የሚቀርቡበት ይሆናል፡፡ ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶች መሰረት የድርሰት ብዛት፣ ድርሰቶቹ የተጻፉበት የቃላት ብዛት፣ የስህተት ብዛት፣ የስህተት ድግግሞሽ እና የትክክለኛነት ተዛማጅነት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

በሰንጠረዥ አንድ በቀረበው መረጃ መሰረት ስህተቶቹ የተቆጠሩት ተጠኚ ተማሪዎቹ በሁለት ጊዜ በጻፏቸው 204 ድርሰቶች ውስጥ ነው፡፡ ድርሰቶቹ የተጻፉት በ12397 ቃላት ሲሆን አንድ ድርሰት በአማካይ 41 ቃላት ይይዛል፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ የተቆጠሩት ስህተቶች ብዛት 1851 ሲሆኑ በአንድ ድርሰት ውስጥ በአማካይ 9.07 ስህተቶች ይገኛሉ፡፡ አንድ መቶ ቃላት የሚይዝ አንድ ድርሰት ውስጥ የሚገኘው የስህተት ድግግሞሽ 21.95 ሲሆን የትክክለኛነት ተዛምዶው 6.69 እንደሆነ መረጃው ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ 4.1 ድርሰቶቹ የተጻፉባቸው ቃላት ብዛት፣ የስህተት ብዛት በመቶኛ፣ አማካይ ስህተት፣ የሰህተት ድግግሞሽና የትክክለኛነት ተዛማጅነት ዝርዝር መረጃዎች

| የድርሰት አይነት | የድርሰት ብዛት | ድርሰቶቹ የተጻፉበት የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የትክክለኛነት ተዛምዶ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድርሰት አንድ | 102 | 5932 | 39.54 | 966 | 52.18 | 4.73 | 11.96 | 6.14 |
| ድርሰት ሁለት | 102 | 6465 | 43.1 | 885 | 47.82 | 4.34 | 10.06 | 7.30 |
| ድርሰት አንድ እና ድርሰት ሁለት | 204 | 12397 | 41.32 | 1851 | 100 | 9.07 | 21.95 | 6.69 |

## 4.2 የስህተቶች ስርጭት

በምዕራፍ ሶስት የድርሰት አተናተን ዘዴ (3.7.2) ላይ እንደተገለፀው ስህተቶቹ በአይነት የተለዩትና የተመደቡት በቅድመ ምደባ የስህተት ምደባ ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም በድርሰቶቹ ውስጥ በብዛት የታዩት ዋና ዋና የስህተት አይነቶች የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት፣ የቋንቋ አወቃቀር ስህተት እና የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ናቸው፡፡ ከነዚህ ዋና ዋና የስህተት አይነት ምድቦች ውስጥ የተቆጠረውን የስህተት መጠን ዝርዝር መረጃ እንደሚከተለው ለማስፈር ተሞክሯል፡፡ በሰንጠረዥ ሁለት በቀረበው መረጃ መሰረት በሁለቱም ድርሰቶች ከተመደቡት የስህተት አይነቶች ከፍተኛ ስህተት የተቆጠረው በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ውስጥ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከተገኙት 1851 ስህተቶች መካከል 912 ያህሎቹ በዚህ ምድብ የተቆጠሩ ስህተቶች ናቸው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 49.27% ሆኗል፡፡ በአንድ ድርሰት ውስጥ የሚገኘው አማካይ የስህተት መጠን 4.39 ሲሆን በአንድ መቶ ቃላት ውስጥ የሚገኘው አማካይ የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 10.98 ይሆናል፡፡ የትክክለኛነት ተዛምዶው 13.00 እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡

ከቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ቀጥሎ ከፍተኛ የስህተት መጠን የተገኘበት ምድብ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ነው፡፡ በሁለቱ ዙር ከተጻፉት ድርሰቶች ውስጥ የተገኘው ስህተት 619 ያህል ነው፡፡ በዚህ ምድብ ውስጥ የተገኘው ስህተት በመቶኛ ሲሰላ 33.44% ይሆናል፡፡ አማካይ የስህተት መጠኑ 3.03 ሲሆን አማካይ ድግግሞሹ 4.98 ሆኗል፡፡ የትክክለኛነት ተዛምዶው ደግሞ 20.01 ነው፡፡ ከቋንቋ አጠቃቀምና ከሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ቀጥሎ ያለውና የመጨረሻውን ደረጃ የያዘው የቋንቋ አወቃቃር ስህተት ነው፡፡ በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ 320 ያህል ስህተቶች ተገኝተዋል፡፡ የዚህ ቁጥር የመቶኛ ስሌቱ 17.28% ነው፡፡ አማካይ የስህተት መጠኑ 1.56 ሲሆን አማካይ የድግግሞሽ መጠኑ ደግሞ 2.56 ይሆናል፡፡ የትክክለኛነት ተዛምዶው 38.76 መሆኑን መረጃው ያረጋግጣል፡፡

ሠንጠረዥ 4.2፡- አጠቃላይ በተጠኚ ተማሪዎች ድርሰቶች ውስጥ በየስህተት አይነት ምድቡ የተፈፀሙ ስህተቶች ብዛት በመቶኛ ፣አማካይ ስህተት፣ ድግግሞሽ፣ የትክክለኛት ተዛማጅነት ዝርዝር መረጃ

| የስህተት አይነት | ድርሰት አንድ | | | | | ድርሰት ሁለት | | | | | ድርሰት አንድ እና ሁለት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት | በመቶኛ | አማካይ | የስህተት | የትክክለ | የስህተት | በመቶኛ | አማካይ | የስህተት | የትክክለ | የስህተት | በመቶኛ | አማካይ | የስህተት | የትክክለ |
| የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት | 484 | 53.07 | 4.39 | 11.10 | 12.26 | 428 | 46.93 | 4.2 | 4.17 | 14.61 | 912 | 49.26 | 4.47 | 10.98 | 13.0 |
| የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት | 312 | 32.55 | 3.06 | 5.26 | 19.00 | 307 | 34.50 | 3.01 | 4.74 | 20.71 | 619 | 33.44 | 3.03 | 4.98 | 20.01 |
| የቋንቋ አወቃቀር ስህተት | 163 | 29.78 | 1.6 | 2.75 | 36.35 | 157 | 17.60 | 1.54 | 2.42 | 41.16 | 320 | 17.28 | 1.56 | 2.56 | 38.76 |
| ድምር | 959 | 100 | 9.4 | 16.16 | 6.18 | 892 | 100 | 8.74 | 13.78 | 6.74 | 1851 | 100 | 9.07 | 14.87 | 6.69 |

## 4.2.1 የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት

በምእራፍ ሁለት መሰረት (2003፣44) እንደተጠቀሰው ከመደበኛ የጽሕፈት ሥርዓት ውጪ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ሀሳብን ከማስተላለፍ የሚገታ ከመሆኑ ባሻገር የመግባባት ሂደትንም ያሰናክላል ብለዋል፡፡ ስለዚህ የአንድን ቋንቋ የአጠቃቀም ሥርዓት ጠብቆ ሀሳብን መግለጽ ወይም ማሰተላለፍ መሰረታዊ የተግባቦት ሂደት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በሠንጠረዥ ሁለት መመልከት እንደሚቻለው ከሶስቱ የስህተት ምድቦች ውስጥ ቀዳሚውን ቁጥር የያዘው የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት እንደሆነ ተገልጿል፡፡ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ባጠቃላይ ከተገኙት 1851 ስህተቶቸ ውስጥ

912(49.27) ያህሉን ቁጥር የያዘ የስህተት ምድብ ነው። የዚህ የሰህተት ምድብ የድግግሞሽ መጠን 10.98 ነው። ይህ ማለት የስህተት አይነቱ በአንድ ድርሰት ውስጥ 10.98 ጊዜ ተደጋግሞ ይገኛል ማለት ነው።

በዚህ አብይ የስህተት ምድብ ውስጥ የተካተቱት ንዑሳን የስህተት ምድቦች የቃላት ድግግሞሽ፣የሆሄያት ግድፈት፣ተገቢ ያልሆነ የሆሄያት ቅርጽ እንዲሁም ኢ-መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም ናቸው። የቋንቋ አጠቃቀም ስንል በድርሰቱ ውስጥ ያሉት ዓረፍተ ነገሮች የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግ የጠበቁ ሆነው በቃላት አጠቃቀም ላይ የተለያዩ ስህተቶች የታዩባቸው ናቸው። የዚህ ምድብ ስህተት ዝርዝር መረጃ በሰንጠረዥ ሶስት እንደሚከተለው ቀርቧል። (አባሪ አራትንይመልከቱ)

ሰንጠረዥ 4.3፡- በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ውስጥ የተፈፀሙ የሰህተት አይነቶች ዝርዝር

| የስህተት አይነቶች | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድ እና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ |
| የቃላት ድግግሞሽ | 28 | 5.78 | 0.27 | 0.46 | 24 | 4.96 | 0.2 | 0.31 | 52 | 5.37 | 0.25 | 0.41 |
| የሆሄያት ግድፈት | 197 | 40.70 | 1.92 | 3.30 | 160 | 33.06 | 1.57 | 2.47 | 357 | 36.88 | 1.75 | 2.87 |
| የሆሄያት ቅርጽ ስህተት | 234 | 48.34 | 2.29 | 3.93 | 224 | 46.28 | 2.19 | 3.45 | 458 | 47.31 | 2.24 | 3.68 |
| ያልተለዩ ስህተቶች | 25 | 5.16 | 0.24 | 0.41 | 20 | 4.12 | 0.2 | 0.31 | 45 | 4.64 | 0.22 | 0.36 |
| ድምር | 484 | 53.07 | 4.39 | 11.10 | 428 | 4.2 | 4.17 | 14.61 | 912 | 49.26 | 4.47 | 10.98 |

## 4.2.1.1 የሆሄያት ቅርጽ ስህተት

ከላይ በሰንጠረዥ ሶስት መመልከት እንደሚቻለው በድርሰቶቹ ውስጥ በፊደላት ቅርጽ (በሆሄያት አጣጣል) ላይ ከፍተኛ የሆነ ስህተት እንደተገኘ ለማወቅ ተችሏል። በድርሰቶቹ ውስጥ በቋንቋ አጠቃቀም ምድብ ውስጥ ከቀረቡት 912 ስህተቶች ውስጥ 458 ያህሉ የተፈፀሙት በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ ነው። የስህተት መጠኑ በመቶኛ ሲሰላ 47.31 ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑ ደግሞ 2.24 ይሆናል። በዚህ ምድብ በአንድ መቶ ቃላት ውስጥ የሚገኘው የድግግሞሽ መጠን 3.68 ይሆናል። ሀሳብን በጽሑፍ ለማስተላለፍ ሲታሰብ የቋንቋው ድምፀ ልሳናት የሚወክሉትን ፊደል በትክክል ለይቶ ማወቅና መጠቀም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ይህን አስመልክተው Byrne (1988:1) የቋንቋው ተናጋሪዎች ትርጉም ሊሰጡ የሚችሉ የንግግር ድምፆችን የሚወክሉ ሆሄያት (ፊደላት) ሥርዓት ባለው መልኩ ተገጣጥመው ቃላትን እንደሚመሰርቱ እና ሀሳቡን በግልጽ ሊያስተላልፉ

እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡ በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ የታዩ ስህተቶች በአማርኛ የፊደል ገበታ ውስጥ የሌለ ቅርጽ ያላቸው “ሆሄያት” በድርሰቶቹ ውስጥ መገኘታቸው እና ሆሄያትን ተገቢ ባልሆነ ቦታ መጠቀም ነው፡፡ እነዚህ ስህተቶች በአብዛኛዎቹ ተጠኚ ተማሪዎች ጽሑፍ ላይ የታዩ ችግሮች ናቸው፡፡ በተለይ ‘ይ’፣ጽ፣ጭ፣ጵ፣ክ በሁሉም ድርሰቶች ውስጥ ቅርጻቸው ተቀይሮ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ሆሄያት በመግደፋቸው ምክንያት አንዳንድ ቃላት ትርጉም አልባ ሆነዋል (አባሪ አራትን ይመልከቱ) እነዚህን ከላይ የቀረቡ ስህተቶች በሶስት ከፍሎ ለማየት ተሞክሯል አንደኛው የሆሄያትን ቅርጽ ሙሉ በሙሉ በመቀየር የተከሰተ ስህተት፣ ሁለተኛው አንዱን ሆሄ በሌላ በመተካት የተፈጠረ ስህተት፣ ሶስተኛው አይነት ስህተት ደግሞ ዲቃላ(ፍንጽቅ) ፊደላትን መጠቀም ባለመቻል የተፈጠሩ ስህተቶች ናቸው፡፡ ከድርሰቶቹ የተወሰዱት ምሳሌዎች ቀጥሎ ቀርበዋል፤ ስህተቶቹንም በቅንፍ ውስጥ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

### ሀ. የሆሄያትን ቅርጽ መቀየር

በዚህ የስህተት አይነት ስር በአብዛኞቹ ሆሄያት ላይ የቅርጽ ስህተት ይታያል፡፡ የ‹ም›፣‹ጅ›፣ ሽ፣ ‹ር›፣ ‹ድ›፣ ‹ጭ›፣ ‹ክ› ወዘተ ሆሄያት ቅርጽ በሁሉም ድርሰቶች ላይ የታየ ችግር ነው፡፡ ሆኖም ለመረጃ ያህል ከሌሎቹ ስህተቶች ጋር በሚከተለው ምሳሌ ተጠቅሰው ይገኛሉ፡፡

- ‹‹…በ(መ)(ጀ)(መ)(ሪ)(ያ) (ይ)ለ(ቀ)(ማ)ል…››
- ‹‹…ማር (ይ)(በ)(ረ)(ዛ)(ል)………፡፡››
- ‹‹…(ጸ)ሎ(ት) (ይ)(ደ)(ረ)(ጋ)(ል)…››
- ‹‹…ስ(ራ)(ም) (ይ)(ሰ)(ራ)(ል)…….››
- “ ……በ(ፋ)ስ ካ(ክ)ርስ(ስ

) ስም የ(ሚ)(ታ)(ወ)(ቅ) ሲሆን…..

- “…..ድሃ…..አር(ዶ) በማብላት (በ)አ(ሉ)(ን)………
- “ ……ሚ(ታ)(ረ)(ደ)ውም (ግ)(ል)()ገ(ል)፡፡

የነዚህ ስህተቶች የታዩት ከ ‘የ’ የፊደል ዘርያ ውስጥ ሳድስ በሆነችው ‘ይ’ በ ‘መ’ ፊደል ዘርያ ውስጥ ደግሞ በሳድሷ ‘ም’ እና ሳብዕ ሆሄ በሆነችው ‘ሞ’ ላይ ነው፡፡ ስህተቶቹ በተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰት ውስጥ በብዛት የታዩ ስህተቶች ናቸው፡፡ ስህተቶቹም የሆሄያቶቹን ቅርጽ ሙሉ በሙሉ ቀይሮ በመጻፍ የተከሰቱ ናቸው፡፡ ከድርሰቶቹ መረጃ መመልከት እንደተቻለው ችግሮቹ ተማሪዎቹ በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ሊያስወግዷቸው ይገቡ የነበሩ ናቸው፡፡

### ለ. ሆሄያትን በሌላ ሆሄ መተካት

ይህ አይነቱ ስህተት የሆሄያትን ቅርጽ ለይቶ ካለማወቅ ወይም ከመደናገር የተፈጠረ ስህተት ይመስላል፡፡

• ስለ ፋስካ

በህል አስመልክቶ ከዚህ ባታች ምጋለጽ ይሆራል፡፡

• ፋስካ መለት ከክርስቲያኖ

ች በህል ውስጥ አንዱ ነው፡፡

• …በየዓመቱ ዙር ያመምመጣ ሲሆን

• ….በፋስካ ወቅት ያምደረጎ ነገሮች ….

• …..በመጀሞር ያለቅሞለ ከዛ ያደርቅለ…..

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የታየው ስህተት ሆሄያትን በመቀየር እንደሆነ ስለአራንፋ በህል አስመልክቶ ከዚህ ባታች ምጋለጽ ይሆራል፡፡" "ስለፋስካ በአል አስመልክቶ ከዚህ በታች የሚገለጽ ይሆናል " ለማለት ተፈልጎ የተፈጠረ ስህተት ነው፡፡ "ፋስካ ማለት

መለት ከክርስቲያኖች በህል ውስጥ አንዱ ነው፡፡ " የሚለው "ፋ ማለት ከክርስቲያኖች በአል ውስጥ አንዱ ነው " ማለት ሲገባው የተፈጠረ ስህተት ነው፡፡ "በየዓመቱ ዙር ያመምመጣ ሲሆን " በየአመቱ ዞሮ የሚመጣ ሲሆን" ማለት

ሲገባው የተከሰተ ስህተት ነው፡፡ እንዲሁም "….በፋስካ ወቅት ያምደረጎ ነገሮች " ተብሎ የተፃፈው "በፋስካ

ወቅት የሚደረጉ ነገሮች " መሆን የነበረበት ተቀይሮ በመጻፉ የተከሰተ ችግር ነው፡፡

**ሐ. የዲቃላ ሆሄያት (ፍንጽቆች) አጠቃቀም**

ሌላው በሆሄያት ቅርጽ የተከሰተው ስህተት ዲቃላ ሆሄያትን (ፍንጽቆችን) ባለመጠቀም የተፈጠረ ነው፡፡ በሚከተለው ምሳሌ የምንመለከታቸው ስህተቶች ‹ኂ› በ‹ሀ›፣ጿ ራብዕ ፊደል በሆነችው ‹ጻ›፣ ‹ኲ› በ‹ከ› ተተክተው እናገኛቸዋለን፡፡

• ከዚያ ቡሀላ ቡና ይቆላል…

• …..ስለ ፋስካ በአል ተገልጻል፡፡

• ….የፋሲካ እለት ጎረቤቶች እንከን አደረሳችሁ ይባባላሉ ፡፡

## 4.2.1.2 ግድፈት

በጥናቱ መረጃ መሰረት ተጠኚ ተማሪዎቹ በድርሰቶቻቸው ውስጥ የገደፏቸው ሆሄያት በመኖራቸው የጽሑፍ ተግባቦቱን እንዳስተጓጎለው ለማየት ተችሏል፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ በቋንቋ አጠቃቀም ምድብ ውስጥ ከቀረቡት 912 ስህተቶች ውስጥ 357 ያህሉ የተፈፀሙት በሆሄያት ግድፈት የስህተት ምድብ ውስጥ ነው፡፡ የስህተት መጠኑ በመቶኛ ሲሰላ 36.88 ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑ ደግሞ 1.75 ይሆናል፡፡ በዚህ ምድብ በአንድ መቶ ቃላት ውስጥ የሚገኘው የድግግሞሽ መጠን 2.87 ይሆናል፡፡ ይህን አስመልክተው Byrne (1988:1) የቋንቋው ተናጋሪዎች ትርጉም ሊሰጡ የሚችሉ የንግግር

ድምፆችን የሚወክሉ ሆሄያት (ፊደላት) ሥርዓት ባለው መልኩ ተገጣጥመው ቃላትን እንደሚመሰርቱ እና ሀሳቡን በግልጽ ሊያስተላልፉ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡ በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ የታዩ ስህተቶች የተለያዩ ሆሄያት በመግደፋቸው ምክንያት አንዳንድ ቃላት ትርጉም አልባ ሆነዋል፡፡ በድርሰቶቹ ከተገኙት ስህተቶች የሚከተሉት ምሳሌዎች ቀርበዋል፡፡ በምሳሌው መመልከት እንደሚቻለው የተገደፉት ሆሄያት በተግባቦት ላይ ከፍተኛ ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ከአውዱ በመነሳት ሀሳቡን እየሞላ ማንበብ ላልቻለ ሰው ችግሩ የከፋ ሊሆን ይችላል፡፡ የተገደፉት ሆሄያት ለምሣሌ ያህል በቅንፍ ውስጥ ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡

1. "……ቡና (ይ)ታጠባል…፡፡"
2. "…..(ከ)ዚያ በኋላ (ከ)በአል ገ(ብ)ቶ ቡና መጠጣት…….፡፡ "
3. "…...በቅድሚያ (የ)ፋስ(ካ) አከባበር (የ)ኢየሱስ ስቅለ(ት)… "
4. "ከ(ዚ)ያን ይቆላል ይወ(ቀ)ጣል…. "
5. "..ውሃ ይጨመራ(ል)…… "

## 4.2.1.3 የቃላት ድግግሞሽ

በቋንቋ አጠቃቀም አብይ የስህተት ምድቦች ውስጥ ከቀረቡት አራት ንዑሳን የስህተት ምድቦች ውስጥ ከታዩ ስህተቶች አንዱ የቃላት ድግግሞሽ ነው፡፡ ድግግሞሹ ከጠቅላላው የስህተት ቁጥር 52 ያህሉን ይዟል፡፡ ይህ የስህተት መጠን በመቶኛ ሲሰላ 5.37% ይሆናል፡፡ አማካይ የስህተት መጠኑ 0.25 ሲሆን ድግግሞሹ ደግሞ 0.41 ነው፡፡ በተጠኚ ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ቃላትን ያላግባብ እየደጋገሙ የመጠቀም ችግር ታይቷል፡፡ እንደዚህ አይነት ስህተት በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ሲከሰት የፅሁፉን ተነባቢነት ከመቀነሱም በላይ ሊተላለፍ የታሰበውን መልእክት ሊያደበዝዘው ይችላል፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ ድግግሞሽ የታየባቸው ዐረፍተ ነገሮች እና ሀረጎች በምሳሌነት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

1. "ዳቦ ይዘጋጃል እንጀራ ይዘጋጃል ዶሮ ይዘጋጃል ክትፎ ይዘጋጃል በቃ ሁሉም ነገር ይዘጋጃል…."
2. "ጠላም ይሰራል ቃሪቦም ይሰራል ፡፡"
3. "….. ጎሮቤት ይጠራል ዘመድ ይጠራል ጓደኛ ይጠራል፡፡ "
4. "ስጋ ይበላል ዶሮ ይበላል ፍያል ይበላል፡፡"
5. "….ከዚያም ይታጠባል ከዚያም ይቆላል ከዚያም ይወቀጣል ከዚያም ጀበና ይታጠባል ከዚያም ውሃ ጀበና ላይ ይጨመራል ከዚያም ጀበና ይፈላል ከዚያም ጎሮቤት ይጠራል……

### 4.2.1.4 ያልተለዩ ስህተቶች

ይህ የስህተት አይነት በብዛት የተከሰተው የአፍ መፍቻ ቋንቋን በጽሑፍ ውስጥ በመጠቀም ነው፡፡ በዚህ የስህተት ምድብ ከአጠቃላዩ የስህተት ብዛት 45 ያህል ስህተቶችን ይዟል፡፡ የመቶኛ ስሌቱ 4.64% ሲሆን አማካዩ ደግሞ 0.22 ይሆናል፡፡ የድግግሞሽ መጠኑም 0.36 ነው፡፡

በዚህ የስህተት ምድብ ስር የታዩ ስህተቶች ምሳሌዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. "…የክርስቲያን ሰው በደመቀ ሁኔታ የምያከብር ኔው…. "
2. "በፋስካ ወቅት ያምደርጎ ነገሮች….. "
3. "ቡነውን እናቆሎለን….. "
4. "ቡና እናጣባሌን… "
5. "ከዛ ብረሚጣዶን እሳት ላይ እናጥዳሌን…. "
6. "…ቡና የቁርስ እንቀርባሌን…. "
7. "…ቡና አአፈላሌ…. "

እነዚህ ምሳሌዎች የንግግር ቋንቋ በጽሑፍ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ እና ጣልቃ ገብነት ያሳያሉ፡፡

### 4.2.2 የቋንቋ አወቃቀር ስህተት

ከንግግር ይልቅ በጽሑፍ የሚተላለፍ መልዕክት የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ሥርዓት መጠበቅ እንዳለበት በምእራፍ አንድ (2.1.3) ተገልጿል፡፡ ተማሪዎች የቋንቋውን አወቃቀር ሥርዓት /ሰዋስው/ በደንብ ካለመረዳት የተነሳ በርካታ ስህተቶችን እንደሚፈጽሙ ገልፀዋል፡፡ በሰንጠረዥ ሶስት ላይ በቀረበው መረጃ መሰረት በአብይ የስህተት ምድብ ከቀረቡት ሶስት የስህተት አይነቶች መካከል በስህተት ብዛቱ መጨረሻ ደረጃ የሚገኘው የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ነው፡፡ ይህ የስህተት ምድብ ባጠቃላይ ከተገኙ 1851 ስህተቶች መካከል 320 ያህል ቁጥር ይዞ ይገኛል፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 17.28% ሆኗል፡፡ አማካይ የስህተት መጠኑ 1.56 ሲሆን በመቶ ቃላት ውስጥ የሚገኘው የስህተት ድግግሞሽ መጠን 2.56 ነው፡፡ በቋንቋ አወቃቀር አብይ የስህተት ምድብ ውስጥ ሶስት ንዑሳን የስህተት ምድቦች ይገኛሉ፡፡ እነሱም የመስተዋድድ አገባብ፣ የዓረፍተ ነገር ስምምነት እና የቃላት አጠቃቀም ስህተት ናቸው፡፡ የዚህን ዝርዝር መረጃ በቀጣዩ ሰንጠረዥ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ሠንጠረዥ 4.4፡- በቋንቋ አወቃቀር የስህተት ምድብ ውስጥ የተፈፀሙ የስህተት አይነቶች ዝርዝር መረጃ

| የስህተት አይነቶች | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድ እና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ |
| የመስተዋድድ እና የተሳቢ አገባብ | 52 | 31.9 | 0.50 | 0.85 | 45 | 28.66 | 0.44 | 0.06 | 97 | 30.31 | 0.47 | 0.75 |
| የዓረፍተ ነገር ስምምነት | 73 | 44.78 | 0.72 | 1.23 | 74 | 47.13 | 0.72 | 1.13 | 147 | 45.94 | 0.72 | 1.18 |
| የቃላት አጠቃቀም | 38 | 23.32 | 0.37 | 0.63 | 38 | 24.21 | 0.37 | 0.59 | 76 | 23.75 | 0.37 | 0.60 |
| ድምር | 163 | 100 | 1.6 | 2.75 | 157 | 100 | 1.53 | 2.42 | 320 | 100 | 1.56 | 2.56 |

## 4.2.2.1 የዓረፍተ ነገር ስምምነት ስህተት

የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ስር ከቀረቡት ንዑሳን የስህተት ምድቦች መካከል የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘው የዓረፍተ ነገር ስምምነት ስህተት ነው፡፡ በአብይ የስህተት ምድቡ ከተፈፀሙት 320 ስህተቶች ውስጥ 147 ያህሉ በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ የተፈፀሙ ስህተቶች ናቸው፡፡ ይህ ቁጥር በመቶኛ ሲሰላ 45.94% ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑ ደግሞ 0.72 ሆኗል፡፡ በመቶ ቃላት ውስጥ የሚገኘው የስህተት ድግግሞሽ ስሌትም 1.18 ነው፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል የተገኙት ስህተቶች የዓረፍተነገር ስምምነቱ መፋለስ የታየባቸው በቁጥር አለመስማማት፣ በፆታ አለመስማማት እንዲሁም በመደብ አለመስማማት ላይ ነው፡፡

**ሀ.የቁጥር ስምምነት ለምሳሌ**

1. ….በግ ፍየል በሬ እና ዶሮ ይገዛል(ሉ)፡፡

2 ……ጎሮቤቶች ይጠራል(ሉ)፡፡

3. ብዙ ሰው(ኦች) ሆነ የሚያከብር ነው….

4. እነዚህ ብቻ አይደሉም ሌላ ብዙ ነገር

ከነዚህ መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎቹ በጽሑፋቸው ውስጥ ስህተት ሊፈጽሙ የቻሉት የዓረፍተ ነገሩን ስማዊ ሐረጎቹ ቁጥር ከግሳዊ ሀረጎቹ ጋር ባለማስማማታቸው ነው፡፡ ስህተቶቹ በነጠላ ቁጥር ባለቤት ጀምረው በብዙ ቁጥር መሰሪያ አንቀጽ ወይም በብዙ ቁጥር ባለቤት ጀምረው በነጠላ ቁጥር መሰሪያ አንጽ የተቋጩ ናቸው፡፡

**ለ. የፆታ እና የመደብ ስምምነት**

በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኝ የመደብ ስምምነት እና የቁጥር ስምምነት በባለቤት እና በማሰሪያ አንቀጽ ትተስስር ይገለጻል፡፡ በተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰት ውስጥ የታዩ ስህተቶችም ይኸው ጉድለት ይታይባቸዋል፡፡ ለምሳሌ

1. “ በመጀመሪያ ቡናው ትቀዳለች”

2. “ቡናው ከፈላ በኋላ እናወጣታለን....”

3. “ክክርስቲያን በአሎች አንዱ እና ታላቁ ፋስካ እንደሆነ ይታወቃሉ”

4. “ የፋሲካ በአል ሁሌም በየአመቱ ትከበራለች...”

በአንደኛው ምሳሌ ላይ የታየው ስህተት “ቡናው እንቀዳለን” የሚለው አረፍተ ነገር ‹‹ቡናው ይቀዳል›› የሚለው ስማዊ ሐረግ እሱ(ነገሩ) በሚል 3ኛ መደብ ፣ተባእት ጾታ፣ ነጠላ ቁጥር የቀረበ ሲሆን ‹‹ ትቀዳለች ››የሚለው ግስ እሷ በሚል 3ኛ መደብ፣ አነስታይ ጾታ፣ ነጠላ ቁጥር ሆኖ በመቅረቡ የተፈጠረ የጾታ ስምምነት ስህተት ነው፡፡ በ2ኛው ምሳሌ የተገኘው ስህተት ‹‹ቡናው››የሚለው የስማዊ ሐረግ ‹እሱ›በሚል ሶስተኛኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባእታይ ጾታ ቀርቦ ሳለ ግሳዊ ሐረጉ ‹‹እናወጣታለን›› የሚለው ግስ ‹እሷ› ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር እንስታይ ጾታ በመቅረቡ የተፈጠረ የጾታ ስምምነት ስህተት ነው፡፡ በ3ኛው ምሳሌ ‹‹በአሎች›› የሚለው የብዙ ቁጥር አመልካች የስማዊ ሐረጉ መዋቅር ‹‹ይታወቃሉ››በሚል ብዙ ቁጥር ማሰሪያ አንቀጽ በመቅረቡ የቁጥር አለመስማማት ስህተት ፈጥሯል፡፡ በ4ኛው ጥያቄ ‹‹..የፋሲካ በአል...››የሚለው ስማዊ ሐረግ እሱ በሚል በሶስተኛ መደብ፣ ተባእት ጾታ እና ነጠላ ቁጥር ቀርቦ ማሰሪያ አንቀጹ ‹‹ትከበራለች...›› እሷ በሚል 3ኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር እና ተባእት ጾታ በመቅረቡ የጾታ ስምምነት ስህተት ተፈጥሯል፡፡

## 4.2.2.2 የመስተዋድድ እና የተሳቢ አገባብ ስህተት

በቋንቋ አወቃቀር አብይ የስህተት ምድብ ውስጥ በስህተት ብዛት በሁለተኛ ደረጃ የምናገኘው የመስተዋድድ አገባብ ስህተትን ነው፡፡ በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ 140 ያህል ስህተቶች ተገኝተዋል፡፡ የመቶኛ ስሌቱ 29.78 % ሆኖ አማካይ ስህተቱ 0.46 ሲሆን የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 0.75 ሊሆን ችሏል፡፡ በዚህ የስህተት ምድብ ስር የታዩት ስህተቶች መስተዋድዶችን በተገቢው ቦታ ባለመጠቀም እና መስተዋድዶችን በመግደፍ የተከሰቱ ናቸው፡፡

**ሀ. የመስተዋድድ አገባብ ስህተት**

በድርሰቶቹ ውስጥ ከታዩት የመስተዋድድ አገባብ ስህተቶች የሚከተሉት በምሳሌነት ተጠቅሰዋል፡፡

1.“የቅድሚያ የፋስካ በአል አከባበር.......”

2. “በበአሉ ታሪክ የሚያመለክተው....... ”

3. “የፋሲካ በአል ሚከበርበት ምክኒያት.....››

4. “....በሶስተኛው ቀን በሞት አሸንፎ ስለተነሳ..... ”

5. “የመጀመሪያ እሳት እናቀጣጥላለን...”

በምሳሌዎቹ ላይ እንደሚታየው ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በመስተዋድድ አጠቃቀም የተለያዩ ስህተቶች ተገኝተዋል፡፡ በምሳሌ አንድ በ ‹በ› ፈንታ ‹የ› በመግባቱ የተፈጠረ

ስህተት ፣በምሳሌ ሁለት በ ‹የ› ፈንታ ‹የ›ን በመጠቀም የተፈጠረ ስህተት፣ በምሳሌ ሶስት ‹የ›ን በመግደፍ የተፈጠረ ስህተት፣በጥያቄ አራት ‹በ›ን ያለአግባብ በመጠቀም የተፈጠረ ስህተት እንዲሁም በምሳሌ አምስት ላይ በ‹በ› ፋንታ ‹የ›ን የበመጠቀም በመጠቀም የተፈጠረ ስህተት ታይቷል።

**ለ.የተሳቢ አገባብ ስህተት**

በድርሰቶቹ ውስጥ የተሳቢ አገባብ ስህተቶች እንደ መስተዋድድ አገባብ ስህተቶች ሁሉ ተሳቢ አመልካችን በተገቢው ቦታ ባለመጠቀም፣ በመግደፍና በሌላ በመተካት የተከሰቱ ስህተቶች ናቸው። ከድርሰቶቹ ውስጥ የተወሰዱት ምሳሌዎች የሚከተለውን ይመስላሉ።

1. "ጀበናው() እሳት ላይ እናደርጋለ(ን) "

2. "ሲኒ እናጥባለ() ቡና ቁርስ እናቀርባለ(ን) ..... "

3. "....ፋሲካ ማለት ጌታች( ) እየሱስ ክርስቶስ ...... "

4. "የአመት በአል ቀን ከደረሰ ኡርጎው(ን) ቅቤው(ን) ተነጥሮ ቁጭ ይደረጋል "

5. "....የአከባቢ ችግርተኞች ልብስ(ን) ካጡ ማልበስ...። "

እነዚህን በምሳሌነት የቀረቡ ዓረፍተ ነገሮች ስንመለከት በሁለት ምክንያቶች ስህተቶቹ ተከስተው እናገኛለን። በተራ ቁጥር 4 እና 5 የቀረቡት ምሳሌዎች የተሳቢ አመልካች የሆነችውን 'ን' በማይገባ ቦታ በመጠቀም የተፈፀሙ ስህተቶ ናቸው። በተራ ቁጥር 1፣2፣3 የቀረቡትን ምሳሌዎች ስንመለከት ስህተቱ የተፈፀመው የተሳቢ አመልካች የሆነችው‹‹ን››በመገደፏ ነው።

## 4.2.2.3 የቃላት አጠቃቀም ስህተት

በቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች ስር ከተመደቡት የስህተት አይነቶች መካከል ሌላኛው የቃላት አጠቃቀም ስህተት መሆኑ ቀደመ ሲል ተጠቁሟል። በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ 113 ያህል ስህተቶች ተገኝተዋል። ይህ ቁጥር በመቶኛ ሲሰላ 24.04% ሲሆን በአንድ ድርሰት የሚገኘው አማካይ ስህተት 0.37% ይሆናል። በመቶ ቃላት ውስጥ ያለው ድግግሞሽ መጠን ደግሞ 0.60 ነው። በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ በተከሰቱ ስህተቶች ውስጥ የታየው ችግር ቃላትን በተገቢው መንገድ በዐረፍተ ነገር ውስጥ ባለመጠቀም ነው። ከድርሰቶቹ ውስጥ የተወሰዱት ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. "በጀበና ከተጨመረ በሓላ ሲኒታጥቦ.... "

2. ".....አመትበአመት አደረሰችሁ "

3. "በአሉ ሲጀመር በቅድሚያ አስር10 ቀን ከተጾመ በኋላ... "

3. "....ሰዎች በግ በማረድ 1/3ሶስተኛውን ለድሃ ቤት በማከፋፈል... ".

እነዚህ ምሳሌዎች ተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰቶቻቸውን ሲጽፉ ሀሳባቸውን በጽሑፍ ለመግለፅ በሞከሩ ጊዜ የቃላት አጠቃቀማቸው እና የሀሳብ ፍሰታቸው ተገቢ ባልሆነ መልክ በመቅረቡ የተፈፀሙ ስህተቶች ናቸው። በምሳሌው ላይ በምሳሌ ቁጥር 1 እና 2 ላይ የታየው ስህተት ‹ ሲኒ ታጥቦ› በማለት

ፈንታ ‹ሲኒታጥቦ›፣‹አመት አመት› በማለት ፈንታ‹አመትበአመት›የሚል ተገቢ ያልሆነ የቃል አጠቃቀም ስህተት ታይቷል፡፡ በምሳሌ 3 እና 4 የታየው ስህተት በቃላት አላስፈላጊ ድግግሞሽ ወይም ድረታ ምክንያት የተፈጠረ ስህተት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡”

### 4.2.3 የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት

በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ሥርዓተነጥብ የምንጠቀመው ለሁለት አላማ ነው፡፡ አንደኛው የምንጽፈው ጽሑፍ ውስጥ ያሉ ቃላት፣ ሀረጋትና ዓረፍተ ነገሮች አሰዳደር ሥርዓትን የጠበቁና ተነባቢ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ሁለተኛው አላማ ደግሞ የጻፍነው ጽሑፍ መልዕክት ለአንባቢያችን በተገቢው መንገድ እንዲደርሰው ለማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን በተገቢው ቦታ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ አለመጠቀም ወይም ፈጽሞ ሥርዓተነጥብ አለመጠቀም የጽሑፉችን መልዕክት ባሰብነው መልኩ ለአንባቢ እንዳይደርስ ምክንያት ይሆናል፤ አንባቢንም ግራ ያጋባል፡፡ ስለዚህ ጸሐፊው የጻፈውን መልዕክት አንባቢ እንዲረዳለት ለማድረግ በተገቢው ቦታ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የአንባቢን የማንበብ ስሜት ሊቀንስ እንደሚችል Dulay.et.al (1982:137) ገልጸዋል፡፡ ሥርዓተነጥቦች የጽሑፍ መሪ ምልክቶች ናቸው፡፡ ይህም ሲባል ጽሕፈት እንደ ንግግር በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ምልክቶች ሊታጀብ አይችልም፡፡ የጽሑፉን መልዕክት ግልጽ ለማድረግ የምንጠቀመው ሥርዓተነጥቦችን ነው፡፡ ስለዚህ ሥርዓተነጥቦች ስንጠቀም በአግባቡና መጠቀም በሚገባን ቦታ ላይ ብቻ መሆን እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህ ጥናት በስህተትነት ከታዩት አብይ የስህተት ምድቦች ውስጥ ከቋንቋ አጠቃቀም ቀጥሎ 619 ያህል ቁጥር ያለው የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ነው፡፡ ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በብዛት የታዩት የአራት ነጥብና የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተቶች ሲሆኑ ቃለ አጋኖ ፣አንድ ነጥብ እና ‹comma›ን በነጠላ ሰረዝና በአራት ነጥብ ተክቶ መጠቀም በድርሰቶቹ ውስጥ የታዩ ዋና ዋና የስህተት አይነቶች ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 4.5፡- በሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ የተፈፀሙ የስህተት አይነቶች ዝርዝር መግለጫ

| የስህተት አይነቶች | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድ እና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ |
| አራት ነጥብ | 204 | 65.38 | 2.00 | 5.06 | 212 | 69.06 | 2.07 | 4.80 | 416 | 67.20 | 2.04 | 4.94 |
| ነጠላ ሰረዝ | 108 | 34.62 | 1.05 | 2.66 | 95 | 30.94 | 0.94 | 2.18 | 203 | 32.80 | 0.99 | 2.39 |
| ድምር | 312 | 100 | 3.06 | 7.74 | 307 | 100 | 3.01 | 6.98 | 619 | 100 | 3.03 | 7.33 |

#### 4.2.3.1 የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት

በሰንጠረዥ አምስት መረጃ መሰረት በሥርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ውስጥ ከተዘረዘሩት ንዑሳን የስህተት ምድቦች የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ከፍተኛውን ቁጥር ይዞ ይገኛል። በድርሰቶቹ ውስጥ ከታዩት 619 የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች መካከል 416 ያህሉ በዚህ ምድብ ውስጥ ይገኛሉ። የዚህ ቁጥር መቶኛ 67.20% ሲሆን አማካይ ስህተቱ 2.04 ነው። በየመቶ ቃላቱ ውስጥ የሚገኘው የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 4.94 ይሆናል። በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ ስህተቶች የታዩት የአረፍተ ነገሮቹ መጨረሻ ላይ አራት ነጥብን ያለመጠቀም እና በአራት ነጥብ ቦታ አንድ ነጥብን መጠቀም የታዩ ስህተቶች ናቸው። በቀረቡት ምስሳሌዎች ሥርዓተ ነጥቦች መግባት ሲኖርባቸው የሌሉበትን ቦታ በቅንፍ ለማመልከት ተሞክሯል።

1. የፋስካ ጊዜ ዘመድና ጎረቤት ይጠራል ( )

2. የተለያዩ ልብሶችን መግዛትና ወዘተ ናቸው( )

3.የፋስካ በአል ሲከበር እያንዳንዱ ሰው ጎረቤቱን ይጠራል ( )

4. ፋሲካ ማለት ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል ያደረገበት ነው( )

5. የፋሲካ በአል አከባበር በክርስትና ሀይማኖት ዘንድ እጅግ ታላቅ እና ደማቅ ነው ( )

ከምሳሌዎቹ መረዳት የሚቻለው ተጠኚ ተማሪዎቹ በጽሑፋቸው ውስጥ አራት ነጥብ መጠቀም ሲገባቸው ባለመጠቀማቸው የፈፀሙትን ስህተት ነው። አራት ነጥብ ባለመጠቀማቸው ምክንያት በአንድ አንቀጽ ውስጥ የጻፉት ሀሳብ የትኛው አረፍተ ነገር የት ተጀምሮ የት እንደሚጨርስ ለመረዳት አዳጋች ይሆናል።

#### 4.2.3.2 የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተት

ነጠላ ሰረዝ በጽሑፍ ውስጥ ያለው አገልግሎት የሚዘረዘሩ ነገሮችን፣ ጥገኛ ዓረፍተ ነገሮችን፣ ተጣማሪዎችን እና የመሳሰሉትን መለየት ነው። በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ ከአጠቃላዩ የስህተት ብዛት ውስጥ 203 ያህል ስህተቶች ተገኝተዋል። የዚህ ቁጥር መቶኛ 32.80% ይሆናል። በአንድ ድርሰት ውስጥ የሚገኘው አማካይ የስህተት መጠን 0.99 ሲሆን በአንድ መቶ ቃላት ውስጥ የሚገኘው የድግግሞሽ መጠን ደግሞ 2.39 ይሆናል። በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ የተከሰቱት ችግሮች ነጠላ ሰረዝን በተገቢው ቦታ ያለመጠቀም እና በነጠላ ሰረዝ ቦታ ‹comma› የመጠቀም ስህተቶች ናቸው። በድርሰቶቹ ውስጥ ከተገኙት ስህተቶች ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ለመጥቀስ ተሞክሯል። በቅንፍ የተቀመጠው ክፍት ቦታ ነጠላ ሰረዝ ሊገባበት የተገባ ነበር።

1. ቡና በመጀመሪያ ይለቀማል ( ) ከዚያ ይደርቃል ( ) በመቀጠል ይወቀጣል ( ) ከዚያ ይበጠራል

2. በመጀመሪያ እሳት ይቀጣጠላል ( ) ከዚያ ቡና ይታጠባል ( ) ቀጥሎ ውሃ ይጣዳል ( ) ከዚያ ቡናው ይወቀጣል....

3. በፋሲካ ወቅት የሚደረጉ ነገሮች እቤትን ማስዋብ ( )ሰውን በመርዳት ( ) የተለያዩ ልብሶችን መግዛት( ) ሥጋ መግዛት...

4. ቡና ጀበና ላይ ይጨመራል ( ) ሰንደል ይገዛል ( ) በክብሪት ይጨራል( ) ጎረቤት ይጠራል ቡናው ይፈላል( ) ከዚያ ይጠጣል ይ....

5. ቤት ይጸዳል( ) እቃ ይታጠባል( ) እንጀራ ይጋገራል( )ጠላ ይጠመቃል( )ዳቦ ይደፋል

አንድ ነጥብን በአራት ነጥብ ፈንታ መጠቀም እና በነጠላ ሰረዝ ፈንታ "comma"ን እና እኩል ይሆናል ምልክትን መጠቀም ለስህተቶቹ መከሰት ምክንያቶች ናቸው፡፡ በመሰረቱ "comma" በእንግሊዘኛውም ቢሆን የነጠላ ሰረዝን ቦታ ሊይዝ ይችላል፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ ከተገኙት ስህተቶች የተወሰዱት ምሳሌዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

1. የፋሲካ በአል አከባበር በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ምክንያት የተጀመረው(.)

2. በመጀመሪያ እሳት ይቀጣጠላል (,) ከዚያም ቡናው ይቆላል(,) ውሃ ይጣዳል(,) ቡናው ይወቀጣል(.)

3.በመጀመሪያ ጥሩ ቡና ከሆነ መምረጥ ያስፈልጋል(.)

4. .... ቡናው ይታጠባል(=) ከዚያ ይቆላል(=) በመቀጠል ይወቀጣል(=) ከዚያ በጀበና ውስጥ ይጨመራል(=)

እነዚህን ከላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች ስንመለከት በተራ ቁጥር አንድና ሁለት ላይ የታየው ስህተት በአራት ነጥብ ፈንታ አንድ ነጥብን በማስገባት የተከሰተ ነው፡፡ በተራ ቁጥር 3፣4 እና 5 ደግሞ በነጠላ ሰረዝ ፈንታ "comma" በመግባቱ ስህተት ሊፈጠር ችሏል፡፡ በአጠቃላይ ሥርዓተነጥቦችን በትክክለኛው ቦታ እና በተገቢ ሁኔታ መጠቀም ለጽሑፍ ተግባቦት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ በተገቢው ሥርዓተነጥብ እየተለየ የተጻፈን ጽሑፍ አንባቢዎች በቀላሉ አንብበው ሊረዱት ይችላሉ፡፡ አንዱ ቃል ከሌላው ተለይቶ ካልተቀመጠ፣ አንዱ አረፍተ ነገር ከሌላው ካልተለየ፣ በምን ስሜትና ምን መልዕክት ማስተላለፍ እንደተፈለገ ካልታወቀ ፣እንዲሁም ትንፋሽ ገታ የሚደረግበት ቦታ ማመልከቻ ካልተገኘ ለማንበብም ሆነ ያነበቡትን ለመረዳት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

## 4.3 የስህተት ምንጭ መላምቶች

በምዕራፍ አራት መግቢያ ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የዚህ ንዑስ ክፍል ትኩረት የሚሆነው ሶስተኛውን መሰረታዊ የጥናት ዓላማ መመለስ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ለተጠኚ ተማሪዎች ከቀረቡ የጽሑፍ መጠይቆች እና ለመምህራን ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች ይተነተናሉ፡፡ በመረጃዎቹ መሰረት በምዕራፍ ሁለት (2.5) ለመግለጽ እንደተሞከረው በኢአፍ-ፈት ተማሪዎች ጽሑፍ ውስጥ በዋናነት የሚታሰቡ የስህተት ምንጮች የተባሉትን ማለትም የመማር ማስተማር

ሂደት ድክመቶች እና የስነልቦናዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎች በተማሪዎች ጽሑፍ ላይ በምን ያህል መጠን ተጽዕኖ እንዳሳደሩ ለመፈተሽ ተሞክሯል።

መረጃዎችን በጽሑፍ መጠይቅ ከተማሪዎች ለመሰብሰብ በአጥኚው የተዘጋጁት ሁለት አበይት ጥያቄዎች ብቻ ናቸው። ጥያቄዎቹም ተማሪዎቹ በጽሑፋቸው ላይ ስህተት በተደጋጋሚ እንደሚፈጽሙ ያውቃሉ? ወይስ አያውቁም? የሚለውን መሰረታዊ ሀሳብ ለመለየት የሚያስችሉ ናቸው። ተማሪዎቹ በጽሑፋቸው ውስጥ ስህተት መፈፀማቸውን ካወቁ ወይም ካመኑ ስህተት ለመፈጸማቸው ምክንያት ይሆናሉ የሚሏቸውን ነገሮች በቀረበላቸው መጠይቅ ውስጥ ባሉት ጥያቄዎች መሰረት ምላሽ ይሰጣሉ። በጽሑፋችን ውስጥ አዘውትሮ ስህተት አይገኝብንም ብለው የሚያምኑ ተማሪዎች ደግሞ ለስኬታቸው ምክንያት ያሏቸውን ነገሮች በቀረበላቸው መጠይቅ ውስጥ ባሉት ጥያቄዎች መሰረት ምላሽ ይሰጣሉ።

በጥናቱ ውስጥ መረጃን ለመሰብሰብ ከተመረጡ 204 ተማሪዎች ውስጥ ድርሰቱን የጻፉት 204 ተማሪዎች ናቸው። ከነዚህ መካከል በጽሑፋቸዉ መካከል ብዙ ስህተት የፈጸሙት 200 (98.04%) ሲሆኑ በጽሑፋቸዉ ብዙ ስህተት ያልተገኘባቸዉ ደግሞ 4 ተማሪዎች (1.96%) ናቸው።

4.3.ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከቀረቡት የጽሑፍ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች ትንተና ከዚህ በታች የሚንመለከተው የዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎችን አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ ስድስት መምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ቀርቦላቸዉ ምላሽ የሰጡትን መረጃ መሰረት በማድረግ የተካሄደውን ትንተና የሚያሳይ ሲሆን፤ እያንዳንዱ የአማርኛ ቋንቋ መምህር 12 ጥያቄዎች ቀርበው ለሁለም ጥያቄዎች ምሽላ ሰጥተዋል። ምላሾቹም ከጥያቄዎቹ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በዝርዝር ማብራሪያ እንደሚከተለው ቀርበዋል። መጠይቅ1 አፋቸውን በጠምባርኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂላቸውን እንዲያሳድጉ ድርሰት አጽፈው ያውቃሉ?" ተብል ለቀረበላቸው ጥያቄ 2 መምህራን የጽህፈት ትግበረው በሚያዛቸው ጊዜ ብቻ ድርሰት እንደሚያጽፉ ሲገልጹ፤ 2 መምህራን ደግሞ አንደንድ ጊዜ በየቤት ስራ መልክ እንደሚያጽፏቸው ገልጸዋል። እንዱሁም ደግሞ 2 መምህራን ተማሪዎቻቸው ድርሰት የመጻፍ ፍላጎት ስለሌቸው ምንም ዓይነት ድርሰት አጽፈው እንደማያውቁ ምላሸቸውን ሰጥተዋል። ስለዚህ በዚህ መረጃ መሰረት መምህራኑ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ለጽህፈት ተግበራት ትኩረት እንደማይሰጡ ያስረደናል።ይሁን እንጂ ተማሪዎቻቸው የጽህፈት ክህል እንዲያዳብሩ ይረዳቸው ዘንድ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የቤት ስራዎችን፣ አሳመንቶችን በመስጠት ተማርዎች ክህላቸውን እንዲያዳብሩ እገዛ ሊያደርጉላቸው እንደሚገባ ነው፡ ከዚህም የተነሳ እነዚህ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ከዚህ በፊት ድርሰት የመጻፍ ልምድ ካለማዳበራቸው የጥናቱ መረጃ እንድሆን በጻፉት ድርሰትም ውስጥ በርካታ ስህተት እንድፈጠር ዋና ምክንያት መሆኑን ያረጋግጣል።

መጠይቅ 2 "ከተማሪዎችዎ መካከል በጠምባርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች

በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ በጻፉት ድርሰት ውስጥ ስህተት ይታያል?" ተብለው ለተጠየቁት የጽሑፍ መጠይቅ 2 መምህራን በቁጥር ይህን ያህል ነው ተብሎ ባይገለጽም ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ በርካታ ስህተቶች አሉ። እነሱም፦ በዓረፍተ ነገሮቻቸው ውስጥ የባላበትና የግስ አለመጣጣም፤ የባላበትና ቁጥር አለመጣጣም፤ሳሊስ ና ሳድስ ፊደላትን ቀያይረዉ እንደሚጠቀሙና ሌሎችም እጅግ በጣም ብዙ ስህተት የሚታይ መሆኑን ሲገልጹ፤ 2 መምህራን ደግሞ ተማሪዎች በሚጽፉቸው ድርሰት ውስጥ የዓረፍተ ነገር ግንባታ ስህተቶች እንደሚፈጽሙ፤የባለቤትና ጾታ አለመጣጣምን ጠቅሰው ተናግረዋል። ከዚህ ባሻገር ደግሞ አንድ መምህር መጠነኛ ስህተት እንደሚታይ ምላሽ ሲሰጡ፤ እንደዚሁም ደግሞ አንድ መምህር በጣም ጥቂት ስህተት ይታያል በማለት ምላሹን ሰጥቷል። ይህ መረጃ እንደሚያመለክተን ግን እነዚህ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት ለድርሰት አጻጻፍ ወሳኝ የሆኑ ነገሮችን የምሲቱ መሆናቸውን ከጽሑፍ መጠይቁ መረዳት ይቻላል። በአጠቃላይ በድርሰት አጻጻፍ ላይ የሚያሳድረው ተጸዕኖ በቀላል የሚታይ አይደለም። መጠይቅ 3 "ተማሪዎችዎ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ ስህተት የሚታይ ከሆነ ምን ዓይነት ስህተት ይመስልዎታል? መንስኤውስ ምን ይመስልዎታል?" ተብለው የተጠየቁ ሲሆን፤ ለዚህም 2 መምህራን የባለቤትና የግስ አለመስማማት፤የአንቀጽ ቅርጽ ጠብቆ አለመጻፍ፤ሀይለ-ቃልንና መዘርዝር ዓረፍተ ነገሮችን ለይቶ በትክክል አለመገንባት ስህተት መሆኑን ሲገልጹ፤ 2 መምህራን ደግሞ የቃላት አጠቃቀም ስህተት እንደሆነ ገልጸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ 2 መምህራን የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት፤ስርዓተ ነጥቦችን በትክክል ቦታቸውን ጠብቆ አለመጠቀም፤የሃሳብ አንድነትና ግጥምጥምነት ችግር በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ከሌሎች ስህተቶች ይበልጥ ጎልቶ የሚታይ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል። በመሆኑም በጠምባርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ከፍተኛውን ብልጫ የያዘ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያረጋግጥልናል። ይህም ከላይ "በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የታዩ ዋና ዋና ስህተቶች" በሚለው ርዕስ ስር በዝርዝር እንደተመለከትነው ተማሪዎቹ በሁለት ዙር በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የፊደላት አጻጻፍና አጠቃቀም፣ የቃላት አመራረጥ፣ አስፈላጊ ያልሆነ ድግግሞሽና ጭመራ የሚሉት መሰረታዊ ስህተቶች እንድከሰቱ ዋና ምክንያት ሲሆን ይታያል። መጠይቅ 4 "ተማሪዎችዎ በአማርኛ ቋንቋ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጠልቃ-ገብነት ይታያል?" ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ስድስቱም መምህራን አዎ ብለው መልስ ሰጥተዋል።ምክንያቱን ስገልጹ ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋና በአፍ-መፍቻ ቋንቋ መካከል ያለውን የሰዋሰው እንድሁም የአናባቢና ተነባቢ ልዩነቶች አለመረዳት ችግር ስላለባቸው በታላሚው ቋንቋ ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጠልቃ እየገባ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሃሳብ መጣረስ ይስተዋላል።ስለዚህም እነዚህ በጠምባርኛ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት

በሚጽፉበት ወቅት በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጠልቃ ገብነት ከፍተኛ መሆኑን ይህ መረጃ ያረጋግጣል፡፡ መረጃውን በመንተራስ እነዚህ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የመምህራኖቻቸው ልዩ እገዛ እንደሚያስፈልጋቸውና የትቶርያል ትምህርት ከአፍ-ፈቶች በተለየ ሁኔታ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ይጠቁመናል፡፡ መጠይቅ 5 "እርስዎስ የጽህፈት ክሂል ለማስተማር የምጠቀሙበትን ዘዴ እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች በክፍል ውስጥ እንደት ይተገብራሉ?" የሚል ሲሆን፤ ለጽሑፍ መጠይቁ ከተመረጡት 6 መምህራን መካከል አንድ መምህር ድርሰት በማጻፍ ለማስተማር የሚጠቀሙበትን ዘዴ በክፍል ውስጥ እንደሚተገብሩ ገልጸዋል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ሁለቱ መምህራን የቤት ስራ በማሰራት፣ ሁለቱ የክፍል ስራ በማሰራት እና አንዱ መምህር ጥያቄ በመጠየቅ ለማስተማር የምጠቀሙበትን ዘዴ በክፍል ውስጥ እንደሚተገብሩ ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ መረጃ መሰረት አብዛኛዎቹ መምህራን ማለትም ከአንደ መምህር በስተቀር ተማሪዎቻቸውን በተለያዩ ጊዜያት ድርሰት በማጻፍ ተማሪዎቹ የጽህፈት ክሂላቸውን እንድያዳብሩ ዕድል የማይሰጡ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በርግጥ ተማርዎችን በክፍል ውስጥ ስለ ጽህፈት ክሂል ወይም ስለ ድርሰት በገለጻ ብቻ መማራቸው ምንም ፋይዳ ሊይኖረው አይችልም፡፡መምህራኑ የተማሪዎቻቸውን የዕውቀት ደረጃቸውን ከግምት በመስገባት የተለያዩ የጽህፈት ተግባራትን በመስጠት ተማሪዎቻቸው ጽፈው የሚያመጡትን በሰአቱ እርማትና ማስተካከያ መሰጠት እንደለበት መረጃው ይጠቁመናል፡፡ በተጨማርም መምህሩ የተለያዩ አጭርና ረዝም ልበ ወለዶችን በክፍል ውስጥ በማምጣት እንድያነቡና እንድጽፉ ቢደረግ የተሻለ ይሆናል፡፡ መጠይቅ 6 "እነዚህ በጠምባርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ ሆሄያትን በትክክል ይጽፋሉ? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ ስድስቱም መረጃ ሰጪ መምህራን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የታላሚውን ቋንቋ ሆሄያት በትክክል እንደማይጽፉ የየራሳቸውን ምክንያት በማስቀመጥ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ በዚህ መሰረት 2 መምህራን ተማሪዎቹ የታላሚውን ቋንቋ ሆሄያት በትክክል የማይጽፉት ቋንቋውን በሚገባ መናገር ካለመቻላቸው የተነሳ እንደሆነ ሲገልጹ፤ 2ቱ ደግሞ የታላሚውን ቋንቋ ሆሄያት በውል ለይተው ስለማያውቁ፤ 1 መምህር ታላሚውን ቋንቋ ለመማር ፍላጎት አለመኖር እንዱሁም 1 መምህር ተማሪዎቹ የሆሄያት ቅርጽ ለይቶ አለማወቅ በማለት ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት አፋቸውን የፈቱበት ቋንቋ ካለመሆኑ የተነሳ አቀላጥፈው መናገርም ሆነ መጻፍ በውል ስለማይችሉ የታላሚውን ቋንቋ ሆሄያት በትክክል ለይተው ድርሰት መጻፍ የሚቸግራቸው መሆኑን ከተገኘው መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በሌላም መልኩ እነዚህ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሆሄያት ቅርጽ መለየት የሚጀምሩት ከ4ኛ ክፍል በመሆኑ በቂ ግንዛቤ ሳይጨብጡ ወደ ቃላትና ሀረጋት ምስረታ እንደሚሸጋገሩ መረጃውን ከሰጡት መምህራን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ሠንጠረዥ 4.6-በታላሚው ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚጠቀሙት የቋንቋ መዋቅር

| ተ.ቁ | የጥያቄዎቹ ዓይነት | የተሰጡ ምላሾች | ምላሽ የሰጡ መምህራን ብዛት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 7 | ተማሪዎችዎ በታላሚው ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ በአብዛኛው የሚከተሉት የየትኛውን ቋንቋ (አፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ወይንስ የታላሚውን ቋንቋ) መዋቅር ነው? | የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን | 6 | 100% |
| | | - | - | - |
| | | - | - | - |
| | | - | - | - |
| ጠቅላላ ድምር | | | 6 | 100% |

# ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያና የመፍትሄ ሐሳብ

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ጠምባርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች መለየት እና የስህተቶቹን ምንጭ መፈተሽ ነው። በዚህ መሰረት በጥናቱ ሊመለሱ የሚገባቸው ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች ተጠቅሰዋል። እነሱም

1. ጠምባርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምን ምን ናቸው?

2. ለስህተቶቹ መከሰት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን ናቸዉ?

3. መፍትሔያቸዉስ ምንድነው ተብለው ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት በተጠኚ ተማሪዎች ከተጻፉ ድርሰቶች እና ከአማርኛ መምህራኖቻቸው ከተሰበሰቡት መጠይቆች የተገኙ መረጃዎችን በመተንተን የሚከተሉት ግኝቶች ላይ ተደርሷል።

በጥናቱ ውጤት መሰረት ጠምባርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ተማሪዎች ሁለት ጊዜ በጻፏቸው 204 ድርሰቶች ውስጥ 1851 ያህል ስህተቶች ተገኝተዋል። የስህተቶቹ አማካይ ስርጭት ሲሰላ 9.07 ሲሆን በመቶ ቃላት ውስጥ የሚገኘው የሰህተት ድግግሞሽ 10.98 መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል።

በዚህ ጥናት ውስጥ ጎልተው የታዩትን የሰህተት አይነቶች በሶስት ምድብ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። እነሱም የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት፣ የቋንቋ አወቃቀር ስህተት እና የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ናቸው። ከሶስቱ የስህተት ምድቦች ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ሲሆን 912 (49.27%) ያህል ሆኗል። ይህ አብይ የስህተት ምድብ የቃላት ድግግሞሽ፣ ግድፈት የሆሔያት ቅርጽ እና ኢ- መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶችን በስሩ አካቶ ይዟል።

በድርሰቶቹ ውስጥ ከተገኙት አጠቃላይ ስህተቶች መካከል በሁለተኛ ደረጃ የምናገኘው የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተትን ይሆናል። በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ የተገኘው የስህተት መጠን 619 (33.44%)ነው። ይህ አብይ የስህተት ምድብ በስሩ የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት እና የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተቶችን አካቷል።

ከሶስቱ አብይ የስህተት ምድቦች ውስጥ የመጨረሻውን ቁጥር የያዘው የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ነው። የስህተት ምድቡ በአጠቃላይ በድርሰቶች ውስጥ ከተገኙት ስህተቶች 320 (17.28%) ያህሉን ይዟል።

በዚህ የስህተት ምድብ ስር ተካተው የሚገኙት ንዑሳን ስህተቶች የመስተዋድድ አገባብ፣ የአረፍተ ነገር ስምምነት እና የቃላት አጠቃቀም ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት ዓላማ መሰረት ጠምባርኛ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ጽሑፋቸው ውስጥ ለሚታዩት ስህተቶቸ ምንጭ ይሆናሉ የተባሉ ምክንያቶችን ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሰረት በተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶችን እና ከመጠይቆች የተገኙ መረጃዎችን በማገናዘብ የተገኙትን ስህተቶች ከሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ጋር ለማያያዝ ተሞክሯል፡፡ እነሱም የመማር ማስተማር ሂደት እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ድክመት እና የስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ተጽዕኖ ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት መረጃ መሰረት የጥናቱ ተተኳሪ ለሆኑት ለጠምባርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ድክመት  የስህተት ምንጭ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይኸውም ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀው መማሪያ መጽሀፍ በተማሪዎቹም ሆነ በመምህራኑ ዘንድ የተማሪዎችን የጽሕፈት ልምድ ለማዳበር ያለው ደርሻ ዝቅተኛ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በተለይ የመጽሀፉ አቀራረብ ሳቢነት የጎደለው፣ ተማሪዎችን የማያሳትፍ እና ድግግሞሽ የበዛበት መሆን ተማሪዎች የራሳቸውን ተሰጥኦ ተጠቅመው የተለያዩ የጽሑፍ ልምምዶችን እንዲያደርጉ ዕድል ያልሰጠ መሆኑን ከተገኙት መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡

ሌላው በዚሁ በመማር ማስተማር ሂደት ስር የታየው ችግር በየትምህርት ቤቶቹ ቋንቋውን ለማስተማር የሚሰጠው ክፍለ ጊዜ በክፍል ደረጃው ከቀረበው ይዘት ጋር ፍፁም የማይጣጣም መሆኑ ነው፡፡ ይህ ችግር መምህራኑ ያላቸውን ችሎታና ልምድ ተጠቅመው ተማሪዎቻቸውን የተሻለ ክህሎት ለማስጨበጥ እንዳይችሉ ተጽዕኖ እንዳሳደረባቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ተማሪዎቹ በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ አጣርተው ሊመጡ የሚገባቸው ስህተት ትኩረት ሳይሰጠው እስከ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ እንዲዘልቅ መሆኑ ሌላው የስህተት ምንጭ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

ለተማሪዎች የስህተት ምንጭ ይሆናሉ ከተባሉት ምክንያቶች ውስጥ ሁለተኛው የስነ- ልቦናዊ ሁኔታዎች ተጽዕኖ ነው፡፡ ስለ ስነ-ልቦና ተጽዕኖ ሁኔታ በምዕራፍ ሁለት (2.5) ለመተንተን እንደተሞከረው የስነ-ልቦና ተጽዕኖ ተማሪዎች ለቋንቋው ያላቸውን ግምት እና የመማር ፍላጎት ሊቀንስ እንደሚችል ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ ተጽእኖ ከሁለት አቅጣጫ ሊመጣ ይችላል፡፡ አንደኛው ተማሪዎቹ ያደጉበት አካባቢ፣ ማህበረሰብ ወይም ቤተሰብ ለቋንቋው ያላቸው አመለካከት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች ቋንቋውን ተምረው ወደፊት እናገኛለን ከሚሉት ትሩፋት ጋር የተያያዘ ነው፡፡

በዚህ ጥናት መረጃ መሰረት ለጠምባርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች የስህተት ምክንያት የሆነው የስነ-ልቦና ተጽዕኖ ምንጩ ተማሪዎቹ “ቋንቋውን ተምረን ነገ የምናገኘው ጥቅም ምንድነው?” ከሚለው

አስተሳሰብ የተነሳ መሆኑን መገምገም ተችሏል። ከተማሪዎች መጠይቆች በተገኙት መረጃዎች መሰረት አብዛኞቹ ተማሪዎች ለቋንቋቸው ፍቅር እንደሌላቸው ፤ የቤተሰብ ወይም የማህበረሰብ ተጽዕኖ እንዳለባቸው ፣ ቋንቋውን ተምረው ወደፊት ሊጠቅማቸው የሚችለውን ነገር ከማሰብ የተነሳ ስልቹ እና ፍላጎት አልባ መሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል።

ከዚህ የተነሳ ተማሪዎቹ ዛሬ ባሉበት የክፍል ደረጃ የሚሰጣቸውን ትምህርት ባግባቡ ለመከታተል አልቻሉም፤ ያሉባቸውን ስህተቶች እና ድክመቶች ለማረም አይነሳሱም፤ አብዛኞቹ ተማሪዎች የሚሰጧቸውን መልመጃዎች እንደግዴታ በመቁጠር ከሞላ ጎደል የሚሞክሩ እንጂ በፍላጎት የሚሰሩ አለመሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

## 5.2 የመፍትሄ ሀሳብ

1. ተማሪዎች በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ እያሉ የፊደላት ቅርጽን፣የቃላት አመሰራረትን እንዲሁም የሥርዓተነጥብ አጠቃቀምን ለይተው እንዲመጡ የሚያግዝ የማስተማሪያ ዘዴና የማስተማሪያ ቁሳቁስ በሚመለከተው አካል ቢዘጋጅ።

2. አጋዥ የአማርኛ ትምህርት የማስተማሪያ ቁሳቁሶች መኖር በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያለውን ክፍተት ሊያሟላ ስለሚችል በየክፍል ደረጃው የሚዘጋጅበት ሁኔታ ቢኖር።

3. የመምህራን የማስተማሪያ ስልት ተማሪዎችን የሚያሳትፍ፣ የሚያዝናና እና ቋንቋውን እንዲወዱ የሚያደርግ ቢሆን።

4. የመልመጃዎች አሰጣጥ ተማሪዎችን የማያሰለች፣ ድግግሞሽ ያልበዛበትና በራሳቸው ተነሳሽነት እንዲሰሩ የሚያደርግ ቢሆን ።

5. በየክፍል ደረጃው የቀረቡትን ይዘቶች በተገቢው ሁኔታ ለማስተማር ተመጣጣኝ ክፍለ ጊዜ ቢሰጥ።

6.ተማሪዎች በቋንቋው ሥነጽሑፍ እና በተለያዩ ቋንቋ ነክ ጉዳዮች ላይ የሚሳተፉበት የሚበረታቱበት ሁኔታ ቢኖር ።

7. የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ተደጋጋፊ ስለሆኑ ተማሪዎች የንባብ ልምዳቸው የሚዳብርበት ሁኔታ በትምህርት ቤቶች ቢመቻች።

ባጠቃላይ በአንድ ነገር ጥሩ ደረጃ ላይ ለመድረስ ፍላጎት እና እውቀት ወሳኝ ነገሮች ናቸው። በጽሕፈትም ጥሩ ደረጃ ላይ ለመድረስ በመጀመሪያ የመጻፍ ፍላጎት ሊኖረን ይገባል። የተማሪዎችን የጽሕፈት ልምድ ለማዳበር ደግሞ አሳታፊ የትምህርት አቀራረብ እና በቂ የልምምድ ጊዜ መኖር አለበት። ይህ ሲሆን ተማሪዎች የሚሰጣቸውን የጽሕፈት መልመጃዎች ለመስራት ያላቸው ዝንባሌ ይጨምራል። ጥሩ ጸሐፊ ለመሆን ጥሩ አንባቢ መሆን ያስፈልጋል ስለዚህ የተማሪዎች የንባብ ባህል የሚዳብርበት ሁኔታ የሚሻሻልበት መንገድ ሊመቻች ይገባል።

## ዋቢ ጽሑፎች


ሀብታሙ አርገታ፡፡(2009)፡፡ "አፋቸውን በሽናሽኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶች ትንተና" በአማርኛ ማስተማር ስነ-ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ህይወት ሎሃ፡፡(2009)፡፡ "በወላይትኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶች ትንተና" ለአማርኛ ማስተማር ስነ-ዘዴ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ልዑልሰገድ አሰፋ፡፡(1987)፡፡ ‹‹በወላይትኛ እና ሲዳምኛ ተናጋሪዎች የአማርኛ ድርሰት ውስጥ የታዩ ስህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና›› የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡(ያልታተመ)

ምህረት ሳዳሞ፡፡(1998)፡፡ ‹‹በዋቻሞ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሀድይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችትንተና፡፡›› የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡(ያልታተመ)

ባየ ይማም፡፡(1987)፡፡ የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፣ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡ ተስፋዬ ሸዋዬ (1981)፡፡ስነልሳን እና ቋንቋን ማስተማር፡፡(ያልታተመ)

ተገኝ አህመድ፡፡(2000)፡፡ ‹‹አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝመምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና፡፡››የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡(1970)፡፡ ‹‹የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት ከ7-12ኛ ክፍል፡፡››ሥርዓተ ትምህርት እና ሱፐርቪዥን መምሪያ በአማርኛ ትምህርት ቡድን የተዘጋጀ፣አዲስ አበባ ፡፡(ያልታተመ)

አለማየሁ ፀጋዬ፡፡(1986)፡፡‹‹በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈጸሙ ዋና ዋና የስህተት አይነቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና፡፡›› የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ፣አዲስ  አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡(ያልታተመ)

አልማዝ ጴጥሮስ፡፡(2011)፡፡ "በከምባትኛ አፍ-ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶች ትንተና" አማርኛን በማስተማር ስነ-ዘዴ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ያለው እንዳወቀ።(2004)። የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ዮናስ አድማሱና ሌሎች።(1966)። አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ የተዘጋጀ። አዲስ አበባ፣ቀደማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ።

Bender M.L and Others. Language in Ethiopia. London; Oxford University press, 1976.

Brown, H.(1994).Principles of Language learning and Teaching. San Francisco: Prentice
Hall.

Byrne, D.(1988).Teaching Writing Skills. Hong Kong: Longman Group Ltd.

Corder,S,P. (1967) " The significance of Language Errors". In J.C.Richards(ed.Error Analisis:Perspectives on second Language Acquistions: London and New york: Language group uk Limited.

Dulay, H .M.Burt,S. Krashen.(1982).Language Two. New York Oxford. Oxford UniversityPress.

Dubin,F. and E. Olshtain (1986) Course Design: Developing Programs and Materials for Language Learning. Cambridge: Cambridge University Press.

Ellis, R.(1989).Understanding Second Language Acquisition. 5thed Oxford: Oxford University Press.

Krashen,S,D.(1987) .Principle and Practice in Second Language Acquisition. New york Prentice Hall International (UK) Ltd.

Littlewood, W.T. (1986) Foreign and Second Language Acquisition Research And its Implication for the Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Norrish H, J. (1983).Language Learners and Their Errors. London and Basingstoke. McMillan Publishers Ltd.

Norrish H, J.(1992).Language Learners and Their Errors. London and Basingstoke McMillan Publishers Ltd.

Richards, J.C and G.P.Sampson.(1992). The tudy of Learning English. In J.C. Richards(ed)Error Analysis Perspectives(3-18) London, Longman group.

Writing skills. London; Longman Group Ltd.

# አባሪዎች

# አባሪ አንድ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

# የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

**በመምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ**

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ የሆናቸው የጠምባርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ትንተና በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል በድህረ ምረቃ መርሀ ግብር አማርኛን በማስተማር ሁለተኛ ድግሪ ለማግኘት ለሚካሄድ ጥናታዊ ጽሁፍ አጋዥ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ መጠይቁ መምህራን ከመለሷቸው የጽሑፍ መጠይቆች የተማሪዎቹን ችግር ነቅሶ በማውጣት የመፍትሔ አቅጣጫዎችን እንደሚጠቁም ይታመናል፡፡ በመሆኑም ለቀረቡት ጥያቄዎች የሚሰጠው ምላሽ ትክክልና አግባብነት ያለው መሆን ከላይ ለተገለጸው ዓላማ መሳካት ጉልህ ሚና ስላለው ይህን ተረድተው ምላሽ በመስጠት እንድተባበሩኝ በሙሉ እምነት ስጠይቅ  ስለሚደረገው ትብብርም በቅድሚያ ለማመስገን እወዳለሁ፡፡

1. ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂላቸውን እንዲያሳድጉ ድርሰት አስጽፈው ያውቃሉ?
2. ከተማሪዎችዎ መካከል አፋቸውን በጠምባርኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ በጻፉት ድርሰት ውስጥ ስህተት ይታያል?
3. በተማሪዎችዎ ድርሰት ውስጥ ስህተት የሚታይ ከሆነ ምን አይነት ስህተት ነው? መንስኤውስ ምን ይመስልዎታል?
4. ተማሪዎችዎ በአማርኛ ቋንቋ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የአፍ-መፍቻ ቋንቋ ጠልቃ ገብነት ይታያል?
5. እርስዎ የጽህፈት ክሂል ለማስተማር የሚጠቀሙበትን ዘዴ እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች በክፍል ውስጥ እንዴት ይተገብራሉ?
6. በጠምባርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ ሆሄያትን በትክክል ይጽፋሉ?

7. እርስዎ ተማሪዎች በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ ለሚታየው ስህተት እርማት ሰጥተው ያውቃሉ?
8. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት የጽህፈት ክሂል ተግባራት ተማሪዎች የጽህፈት ክሂላቸውን እንዲያጎለብቱ ከማድረግ አንጻር ያለው ሚና ምን ይመስልዎታል?
9. ተማሪዎችዎ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የታላሚው ቋንቋ ሰዋስው (የነጠላና የብዙ ቁጥር ስምምነት፣ የባለቤትና የግስ ስምምነት---) ጠብቀው ይጽፉሉ ብለው ያምናሉ?
10. ተማሪዎችዎ በተለያዩ ጊዜያት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በአብዛኛው ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸውና ከታላሚው ቋንቋ በየትኛው ለማከናወን ይሻሉ?
11. ተማሪዎችዎ በታላሚው ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ በአብዛኛው የሚከተሉት የአፍ-መፍቻ ቋንቋ ነው ወይስ የታላሚው ቋንቋ መዋቅር ነው?
12. እነዚህ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ የሆናቸው ተማሪዎች በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ በአብዛኛው የሚጠቀሙት ረጃጅም አረፍተ ነገሮችን ነው ወይንስ አጫጭር ዓረፍተ ነገሮችን?

*አመሰግናለሁ!!*

አባሪ ሁለት

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የዚህ ፈተና ዋና ዓላማ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ የሆናቸው የጠምባርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ትንተና በሚል ርዕስ ለሚደረግ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው። በመሆኑም ከታች የቀረቡትን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ የሚትጽፉት ድርሰት ከላይ ለተገለጸው ዓላማ መሳካት ጉልህ ሚና ስላለው ይህን ተረድተው እንድተባበሩኝ በሙሉ እምነት ስጠይቅ ስለሚደረገው ትብብርም በቅድሚያ ለማመስገን እወዳለሁ።

**የአንቀጽ መጻፊያ ቅጽ**

**የአንቀጽ መጻፊያ ርዕሶች (የመጀመሪያ ዙር)**

1. የጎጆ ቤት አሰራር
2. የደገሌ አድባር ምንነት

ርዕስ፡- ________________________

የተጠኚ/ዋ ተማሪ ኮድ፡-_________

________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
__________________________

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የዚህ ፈተና ዋና ዓላማ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ የሆናቸው የጠምባርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ትንተና በሚል ርዕስ ለሚደረግ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው። በመሆኑም ከታች የቀረቡትን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ የሚትጽፉት ድርሰት ከላይ ለተገለጸው ዓላማ መሳካት ጉልህ ሚና ስላለው ይህን ተረድተው እንድተባበሩኝ በሙሉ እምነት ስጠይቅ ስለሚደረገው ትብብርም በቅድሚያ ለማመስገን እወዳለሁ።

**የአንቀጽ መጻፊያ ቅጽ**

**ቀጥሎ ከቀረቡት ርዕሶች የሚስማማችሁን በመምረጥ ድርሰት ጻፉ።**

**የአንቀጽ መጻፊያ ርዕሶች (የሁለተኛ ዙር)**

1. ገንዘብ ይሻላል ወይስ እውቀት?
2. መምህር መሆን ይሻላል ወይስ ወታደር?
3. የገጠር ኑሮ ወይስ የከተማ ይሻላል?
4. የቡና አፈላል ሂደት
5. ባህላዊ ጋብቻ
6. ግብር መክፈል
7. የእንጀራ አዘገጃጀት
8. የደብዳቤ ጥቅም
9. የፋስካ በዓል አከባበር ምንነት

ርዕስ፡- ______________________

የተጠኚ/ዋ ተማሪ ኮድ፡-________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________

# አባሪ ሶስት

## ለተማሪዎች የቀረበ የድርሰት ፈተና



















# የአጥኚው ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተጠቀሰው ይህ ጥናት የግሌ ሥራ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡ ዓለምአቀፋዊ ተቀባይነት እንዳላቸው ልምዶች መሠረት በጥናቴ ውስጥ የተጠቀሙኩባቸውን ጽሁፎች በሙሉ በዋቢ መጽሐፍት ሥር በማስቀመጥ ዋጋ ሰጥቻቸዋለው፡፡ የሌላውን ሰው ሥራዎች ሳያመሰግኑ ወስዶ መጠቀም በዩኒቨርሲቲ ህግ እንደሚያስቀጣና የአእምሮ ንብረት ሌብነት መሆኑን በደንብ አውቃለሁ፡፡ ስለዚህም የተጠቀምኩባቸውን ሥራዎች በሙሉ በዋቢ መጽሐፍት ሥር ዋጋ ሰጥቻቸዋለው፡፡

የአጥኚው ስም፡-_ዘካርያስ ኢሳያስ_

ፊርማ፡- ---------------------------